# ስላሴ በቁርዓን

## ሀ. ቁርዓን ስለ ስላሴ ትምህርት ምን ይላል።

በቁርዓን የተገለጠው የሥላሴ ትምህርት የክርስትያኖችን አስተምሕሮ አይደለም። የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ /እርሷም/ አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ በእርሱም ምንንም ላናጋራ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጉ ላይገዝ ነው በላቸው ሱራ3፥64

እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ በአላህም ላይ እውነት እንጂ ውሸትን አትናገሩ የመሪየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም መጣላት ቃሉም ከሱ የኾነ መንፈስ ብቻ ነው። በአላህና በመልክተኞቹ እምኑ አማልክት/ሦስት ናቸው አትበሉ ምክንያቱም ለናንተ የተሻለ ይኾነልናል አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው ። ለርሱ ልጅ ያለው ከመኾን የጠራ ነው። ሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው መመኪያም በአላህ በቃ።ሱራ 4፥171

እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ አልመሲሕም አለ የእስራኤል ልጆች ሆይ ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ። እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በእርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮች ምንም ረዳት የላቸውም የሚለው የቁርዓን ጥቅስ ለምህረት ምንም በር እንደ ሌለው የሚያሳይ ነው።

ልጆቼ ሆይ ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሰሩ ብዬ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው ኃጢአት ቢሰራ በአብ ዘንድ ጠብቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኃጢአታችንም የሚደመሰሰው በእርሱ ነው። 1ዮሐ. 2፥1-2 ቁርዓን ለበዳዮች ረዳት የላቸውም ስል መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለበዳዮች ረዳት አላቸው ይላል።

እርስዋ ወንድ ልጅ ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ስለሚያድናቸው ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ማቴ. 1፥21

እነዚያ አላህ ሦስት ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አስማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል:: ወደ አላህ አይመለሱምና ምህረትን አይለምኑትም? አላህ መሐሪ አዛኝ ነው የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች እንጂ ሌላ አይደለም:: እናቱም በጣም እውነተኛ ናት::/ሁለቱም/ምግብን የሚበሉ ነበሩ አንቀጾችም ለእነርሱም / ለከሐድዎች/ እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከቱ:: ሱራ 72-75

የመርየም ልጅ አልመሲሕ በፊት እንደ ነበሩ አገልጋይ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህ ማለት አምላክ አይደለም ማለት ነው:: ሙስሊም ወንድሞቻችን እናምነዋለን የሚሉት ኢንጂል/ወንጌል/ እንዲህ ይላል ቃል በመጀመሪያ ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ይህም ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ:: እርሱ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ ከተፈጠረውም ሁሉ አንድም ነገር ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም:: በእርሱ ሕይወት ነበረች ይህች ሕይወት የሰዎች ብርሀን ነበረች ብርሀን ጨለማ ያበራል ጨለማ ብርሃንን ከቶ አላሸነፈውም:: ዮሐ. 1፥1-5

አላህም የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎች እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃል? በሚለው ጊዜ /አስታውስ/ጥራት ይገባህ ለኔ ተጋቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ አውቀኸዋል በነፍሴ ውስጥ ያለው ሁሉ ታውቃለህ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል:: በርሱ ያዘዘኸኝን ቃል ጌታየንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለት እንጂ

ለነርሱ ሌላ አላልኩም በውስጣቸውም እስካሁን ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፣ በተሞላኸኝም ጊዜ/ባነሳኸኝ ጊዜ/ አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ :: ሱራ 5፥116-117

እንደ ቁርዓን አገላለፅ አላህ ለዒሳ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ እኔን እና እናቴን ሁለት አምላክ አድርጋችሁ ያዙ ብለሀልን? ጌታ ኢየሱስ ደግሞ እኔ አላልኩም የሚል መልስ ሰጥቶአል በመጀመሪያ ደረጃ ወንጌል ኢየሱስን የመርየም ልጅ ሳይሆን የሚለው የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ነው የሚጠራው መልአኩም እንዲህ አላት ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝተሻል አትፍሪ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ሉቃ. 1፥30-32 የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን ሙሉ ሀሳብ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ በሚለው ርዕስ ተመልክተነዋል:: በአንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም አንተ በእኔ ዘንድ ያለውን ታውቃለህ የሚለው ከኢንጅል እውነት ጋር በጣም የሚቃረን ነው:: መለኮትነታቸውና አንድነታቸው እንዲህ ተገልጧል ፊሊጶስም ጌታሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፊሊጶስ ሆይ ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል ታድያ አንተ አብን (አላህን) አሳየን እንዴት ትላለህ?እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? ለእናንተ የሚናገረው ቃል የምናገረው በራሴ ስልጣን አይደለም ነገር ግን ሥራውን ሁሉ የምሰራው በእኔ የሚኖረው አብ (አላህ) ነው እኔ በአብ(አላህ) እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ አለዚያ በስራዎቼ ምክንያት እመኑኝ:: ዮሐ. 14፥8-11

አሁን ካነበብነው ቃል ተነስተን ለምንድን ነው? ደቀመዛመርቱ እንኳን በግልፅ ያላወቁት ሰው ሁሉ ግራ የተጋባው፡ ምክንያቱ ጌታ መልእክተኛ ሆኖ በመምጣቱ ነው፡፡ አይሁዳውያን የመሲሕን መምጣት የሚጠብቁት በኢየሩሳሌም በነገስታት ግቢ ይወለዳል ብለው ነው፡፡ እርሱ በከብቶች በረት ተወለደ አመጣጡ ራሱን የቻለ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

ሙስሊሞች መሲሕ መወለዱ ያምናሉ ያውቃሉም እንዲያውም በቁርዓን ተፅፎአል አይሁዶች ግን አልተወለደም ገና ይወለዳል ብለው ይጠብቃሉ፡፡

ስለ ጌታ ለሰዎች በምንናገርበት ጊዜ እንግዳ የሆነ ጥያቄ ቢጠይቁ አትደነቁ ምክንያቱም የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ጥያቄ እየጠየቁ በውስጣቸው የነበረው ጥያቄ ሳይመለስ እኛ የሙሴ ደቀመዝሙር ነን የራሳችን ሃይማኖት አለን እንዳሉ እውነትን ሳያውቁ በሞት ተወስደዋል፡፡ የወንጌልን እውነት ለማወቅ እንደ አይሁዳውያን አስቀድሞ ልብን መዝጋት ሳይሆን የሚያስፈልገው እንደ ቤርያ ሰዎች በልብ ሥፋት ወንጌልን ሰምቶ በጌታ በኢየሱስ አምኖ የዘላለም ሕይወት ማግኘት ነው ትልቁ ቁም ነገር፡፡

ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጽሐፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ፡፡ ስለዚህም ከእነርሱ ብዙ ከግሪኮችም የከበሩት ሴቶችና ወንዶች ጥቂት ያይደሉ አመኑ፡፡ ሐዋ. 17፥10-12

በቁርዓን እንደ ተገለፀው ክርስቲያኖች ሦስት አምላክ ያመልካሉ ብለው የሚሉአቸው አብ ወልድ ማርያምን ነው፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮ አይደለም ሙስሊሞች ክርስቲያኖች

ሦስት አምላክ ያመልካሉ የሚሉት ከዚህ ተነስተው ነው። አብና ወልድ በአዳም አፈጣጠር ላይ የነበራቸው ድርሻ ከሚቀጥለው የቁርዓን ጥቅስ ይምልከቱ።

ይህ ከታምራቶችና ጥበብን ከያዘው ተግሳፅ ሲኾን በአንተ ላይ እናነበዋለን። አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው ከአፈር ፈጠርነው ከዚያም ለእርሱ ሰው ኹን አልነው ኾነም ።ሱራ 3፥58-59 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ሰዎችም በባህር ውስጥ በሚኖሩ ዓሳዎች በሰማይ በሚኖሩ ወፎች በእንስሳትና በምድር ላይ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች እንዲሁም በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው አለ። ዘፍ. 1፥26

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ከመሬት አፈር ወስዶ ሰውን ከአፈር አበጀው በአፍንጫውም ሕይወት የሚሰጥ እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሆነ።እግዚአብሔር አምላክ በምስራቅ በኩል በኤደን የአትክልት ቦታን አዘጋጀ የፈጠረውን ሰው በዚያ እንዲኖር አደረገው ዘፍ. 2፥7-8 በሰው አፈጣጠር ቁርዓን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል ቁርዓን የሰው አፈጣጠር በሚገልፅበት ጊዜ ሰሪዎቹ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ መሆናቸው ሲገለፅ ከአፈር ፈጠርነው ከዚያም ለእርሱ ሰው ኹን አልነው ኾነም።

እነዚህ አላህ እርሱ አልመሲሕ የመርየም ልጅ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ የመርየም ልጅ አልመሲህን እናቱንም በምድር ያለን ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማን ነው? በላቸው። የሰማይና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው የሚሻውን ይፈጥራል። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

ሱራ 5፥17

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ዒሳ አምላክ መሆኑን ለዘመኑ ፍፃሜ እንደሌለው ይናገራል:: በተጨማሪም ተመልሶ ይመጣል ስመጣ ሁሉም ሰው ያየዋል:: እነሆ በደመና ይመጣል የወጉት ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ ሰው ሁሉ ያየዋል የምድር ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ምክንያት ያለቅሳሉ አዎን ይህ ነገር እውነት ነው አሜን:: ያለው የነበረው የሚመጣውም ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር አምላክ አልፋና አሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ ይላል:: ዮሐ. ራዕይ 1÷7-8

አይሁድ ዑዘይር /እዝራ/ የአላህ ልጅ ነው አለች:: ክርስቲያንኖች አልመሲህ ዒሳ የአላህ ልጅ ነው አሉ ይህ በአፎቻቸው /የሚናገሩት/ ቃላቸው ነው:: የዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ:: ሱራ 9÷30 ኢንጂል እንዲህ ይላል:: እግዚአብሔርን ያየው ከቶ ማንም የለም ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንዱ ልጁ ብቻ ገልጦታል:: ዮሐ. 1÷18

የመርየም ልጅ ምሳሌ በተደረገ ጊዜ ሕዝቦች/ከሐዲዎች/ ወዲያውኑ በእርሱ ይስቃሉ:: አማልክቶቻችን ይበልጣሉን? ወይስ እርሱ አሉም ለክርክርም እንጂ ላንተ እርሱን ምሳሌ አላደረጉም:: እውነት እነርሱ ክርክረ ብርቱ ሕዝቦች ናቸው እርሱ በርሱ ላይ የለገስንበት ለእራኤል ልጆች ተአምር ያደረግነው የኾነ ባሪያ እንጂ ሌላ አይደለም ብንሻም ኑሮ በምድር ላይ ከናንተ ምትክ መላእክትን ባደረግን ነበር:: እርሱ ዒሳ ለሰዓቲቱ ማወቅያ በእርግጥ ምልክት ነው:: በርሷም አትጠራጠሩ ተከተሉኝም ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው በላቸው ሰይጣንም አያግዳችሁ ግልፅ ጠላት ነውና ዒሳ በተዓምራትቶች በመጣ ጊዜ አላቸው በእርግጥ በጥበብ መጣሁላችሁ የዚያንም በርሱ የምትለያዩበት ከፊሉን ለናንተ ላብራራላችሁ መጣሁ አላህንም ፍሩ ታዘዙኝም:: አላህ ጌታዬ ጌታችሁ ነውና ተገዙለት ከነርሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ስኾን ከመጽሐፉ መኾኑን

እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ:: እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ:: እነርሱም የሚያውቁት ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ::ማንም ሰው ከአላህ መጽሐፍንና ጥበብን ነቢያትንም ሊሰጠውና ከዚያም ለሰዎች ከአላህ ሌላ ባሮች ኹኑ ሊል አገባውም ግን መጽሐፍን የምታስተምሩ በነበራችሁትና የምታጠኑም በነበራችሁት በእውቀታችሁ ሰዎች ኹኑ ይላቸዋል::

ሙስሊሞች ከጥንት ጀምሮ ክርስቲያኖች ብዙ አምላኮች ያመልካሉ ይላሉ ይህ አስተሳሰብ ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም የምናመልከው አንድ እግዚአብሔር ነው:: ጅማሬና ፍፃሜ የሌለውን ስሙ ከፍ ያለ ነው ልዩ አምላክ ክብሩን ለማንም የማያጋራ ነው::እኛ ም ይህን እናውቃለን::እርሱ እግዚአብሔር ነው::ሌላ አምላክ የለም:: እግዚአብሔር መንፈስ ነው ወሰን የለውም ዘላለማዊ ሁሉን አድራጊ ሁሉን ቻይ ቅዱስ ጻድቅ እውነተኛ ነው:: እርሱ ከሁሉም በላይ ከፍ ያለ ነው የማይለዋወጥ የማይከፋፈል የማይለያይ አምላክ ነው::

የእግዚአብሔር አንድነት በቅዱሳት መጽሐፍት እንዲህ ተገልጿል እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው:: ዘዳ. 6፥4 እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜም ይህ ነው ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬም ለጣዖት አልሰጥም ኢሳ.42፥8 ለእኛ ግን ሁሉም ነገር ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆነ አንድ አምላክ አብ አለን ደግሞም ሁሉም ነገር በእርሱ አማካይነት የሆነ እኛ በእርሱ አማካይነት የሆነ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን:: 1ቆሮ. 8፥6

በእርግጥ ክርስቲያኖች የሚያምኑት እግዚአብሔር ያዘጋጀው ያስተጋባው ክርስቶስ በትምህርቱ የገለፀው የእግዚአብሔር ስም አንድ ነው የማይለያይ የማይነጣጠል የማይዛባ ዘላለማዊነት በሦስት ሥብዕና ተገልፆአል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ:: እግዚአብሔር በህያው ቃሉ አማካይነት ራሱን የገለፀው ቃል

ወልድ/ኢሳ/ መንፈሱ ዳግም መንፈስ ቅዱስ በመባል ይጠራል። ይህ አንድነት ሦስት የራሳቸው ማንነት ያላቸው አካላት ግን ደግሞ የማይለያይ የማይነጣጠል ማንነት አላቸው።

እስልምና የክርስቲና አስተምህሮ ስህተት ነው ይላል ሙስሊም ወገኖቻችን ትምህርቱን ቀረብ ብለው ሳይረዱ ትምህርታቸው ትክክል አይደለም ማለት የለባቸውም እውነተኛው የሥላሴ አስተምሮ የብዙ አማልክት አምልኮ አካላዊ መባዛትን አያስተምርም።

ለሙስሊም ወገኖቻችን ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ እስ ይኸውም እስልምና ገና በመስፋፋት ሳለ የስህተት ትምህርት ይዘው የተነሱ ሰዎች ነበሩ የሥላሴ አስተምሮአቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አብ ወልድ ማርያም የሚል ትምህርት ይዘው ተነስተው ነበር።ይህን መስማት በመስፋፋት ላይ ለነበረውና አንድ አምላክ ብሎ ለተነሣው እስልምና ትልቅ ስድብ ነው።ለእስልምና ብቻ ሳይሆን ለክርስቲናም ጭምር አሳፋሪና መነገር የሌለበት የሥላሴ አስተምህሮ ነው። ሙስልም ህብረተሰብ የሚያውቀው የሥላሴ አስተምህሮ ይህን ይመስላል።

በዚህ በያዝውነው ዓመት አንድ ወጣት ሙስሊም ያለው ይህን ያረጋግጥልናል። ሥራ ፍለጋ ወደ ሳውድ አረቢያ ሄዶ ኑሮውን በዚያ አድርጓል የሳውዲ አረቢያ ህዝብ ሱኒ የሚባለውን የእምነት ክፍል ነው የሚከተለው ዝሙት ሌብነት እነዚህና ሌሎችም ሲያደርግ የተገኘ በሞት ይቀጣል ከሙሴ ህግ በቀጥታ የተወሰደ ነው። መጠጥ መጠጣት ጫት መቃም ለሰው አምልኮ እና ስግደት መስጠት ሰው ከሞተ በኋላ ወደ ገነት ለማስገባት የሚደረገው ሥርዓት ይቃወማል።

ይህ ወጣት ወደ ሀገር ቤት ቤተሰቡን ለመጠየቅ በመጣ ጊዜ የተናገረው ብዙዎችን አስደንግጧል እናንተ ሙስሊሞች አይደላችሁም

ከእናንተ ይልቅ ሦስት አምላክ አለን የሚሉ ማርያም ኢየሱስ /ዒሳ/ አላህን የሚያምኑ ይሻላሉ። እናንተ ባዕድ አምላኪዎች ናችሁ ለእንጨትና ለድንጋይ ከሚሰግዱ በምንም አትለዩም አላቸው። ወጣቱ እንዳለው እስከ አሁን በሙስልሙ ህብረተሰብ የሚታወቀው የሥላሴ ትምህርት አብ ወልድ ማርያምን ነው።

በቁርዓን ለጌታ ኢየሱስ /ዒሳ/ የቀረበ ጥያቄ አለ አላህም የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎች እኔና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሀል በሚለው? ጊዜ /አስታውስ/ ጥራት ይገባሕ ለኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት አይገባኝም ብየው እንደኾነም በእርግጥ አውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም አዋቂ አንተ ብቻ ነህና በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታየንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለት እንጂ ለእነርሱ ምንም አላልኩም በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በእነርሱ ተጠባባቂ ነበርኩ በተሞላኸኝም ጊዜ/ባነሳኸኝም ጊዜ/ አንተ በእነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ አንተ በነገረ ሁሉ አዋቂ ነህ።

አይሁዶችም ይህን መሰል ቁጣ የተቆጡበት ጊዜ ነበር አይሁዳውያንም በቁርዓን የተጠየቀውን ዓይነት ጥያቄ ጠይቀውታል አይሁዳውያን በዙሪያው ተሰብስበው እስከ መቼ በጥርጣሬ ታቆየናለህ አንተ መሲህ እንደ ሆንህ በግልጥ ንገረን አሉት ኢየሱስ እንዲህ ስል መለሰላቸው እኔ ነግሬአችኋለሁ እናንተ ግን አታምኑም በአባቴ ስም የምሰራው ሥራ ስለ እኔ ይመሰክራል።እናንተ ግን ከበጎቼ መንጋ ስላልሆናችሁ አታምኑም በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ። እኔም አውቃቸዋለሁ እነርሱም ይከተሉኛል። እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣችኋለሁ ። ስለዚህ ከቶ አይጠፉም ከእኔ እጅ ማንም ነጥቆ አይወስዳቸውም። እነርሱን ለእኔ የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል።

ከአብ እጅ እነርሱን ነጥቆ መውሰድ የሚችል ማንም የለም። እኔና አብ አንድ ነን።

በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን ኢየሱስን ለመውገር እንደገና ድንጋይ አነሱ። ኢየሱስም ከአብ የተሰጠኝ ብዙ መልካም ሥራዎች አሳየኋችሁ ታዲያ የምትወግሩኝ ስለየትኛው ሥራዬ ነው? አላቸው።

እነርሱም እኛ የምንወግርህ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ስለመናገርህ ነው እንጂ ስለ መልካም ሥራህ አይደለም እንዲሁም አንተ ሰው ሆነህ ሳለ ራስህን አምላክ ስለ አደረግህ ነው። ሲሉ መለሰለት።

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው በሕጋችሁስ እናንተ አማልክት ናችሁ አልሁ የሚል ተጽፎ የለምን የእግዚአብሔር ቃል የማይሻር መሆኑ የታወቀ ነው። እንግዲህ እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመሰጣቸውን ሁሉ አማልክት ብሎ ጠርቶአቸዋል። ታዲያ አብ የቀደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላለ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ትናገራለህ ትሉታላችሁን? እኔ የአባቴን ሥራ የማልሰራ ከሆንሁ አትመኑኝ። የአባቴን ሥራ የምሠራ ከሆንሁ ግን በእኔ እንኳ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ። በዚህ አይነት አብ በእኔ እንደሆነና እኔም በአብ እንደሆንሁ በሚገባ ታውቃላችሁ።

እነርሱ እንደገና ሊይዙት ፈለጉ እርሱ ግን ከእጃቸው አምልጦ ሄደ። ዮሐ. 10፥24-39 በጊዜው የተለያዩ የስህተት ትምህርቶች ተነስተው ነበር በተለይም ቤቴክርስቲያን ያወገዘችው የሁለት አማልክት አምልኮን ነው ። ትምህርቱ በእስልምናም ተወግዞአል የመጀመሪያው አምላክ የብርሃን አምላክ መልካም አምላክ የመልካም ነገር ሁሉ መገኛ ነው ብለው ያምኑ ነበር።

ሁለተኛው የጨለማ አምላክ የክፋት ሁሉ ምንጭ የመጥፎ ነገር መገኛ አምላክ እንዳለ ያምኑ ነበር። በጊዜው በደረሱበት መረዳት

ጨለማ ብርሃንን ተክቶ ለመስልጠን አዛዥ አለው ሞት በሰው ላይ እንዲሰለጥን የሚያደርገው የሞት አምላክ ነው::በሽታ ጥላቻ እርስ በርስ መገዳደል እነዚህና ሌሎችም በሰው ዘር የሚደርሱ አደጋዎች ምንጫቸው የክፋት አምላክ እንደሆነ ይታመን ነበር::

ስለ ብርሃንና ጨለማ አመጣጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ በዚያን ጊዜ ምድር ቅርፅ የሌለባት ባዶ ነበረች ጨለማም በጥልቁ /ውቅያኖስ/ ላይ ነበር:: የእግዚአብሔር መንፈስ በውሀ ላይ ይሰፍ ነበር:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሔርም ብርሃን መልካም ነገር መሆኑን ተመለከተ ስለዚህ እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ ለየ:: ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ሰየመው::

ስለ ጨለማና ብርሃን አመጣጥ ከማየታችን በፊት በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሚለውን እንመልከት በጌታ በኢየሱስ አምነው ዳግም የተወለዱ ምንም ነገር ከማድረጋቸው በፊት እግዚአብሔርን ማስቀደም እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ መልዕክት ይዞአል::

ዳዊት በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሚለው መርሆ በህይወቱ ተግባራዊ በማድረጉ የእንበሳውን የጀርባ አጥንት ሰብሮአል ድቡን መትቶ በመጣበት መልሶታል እግዚአብሔር በፊቱ ወጥቶ የሰጠውን ድል እንግዲህ ገልፆታል እግዚአብሔር በጣላቶቼ መካከል እንደጉርፍ ሰባብሮ ገባ ብሎአል:: እግዚአብሔር ከአማኝ ፊት ቀድሞ ሲወጣ እንደተራራ የሆነ ችግር ይናዳል ምድረ በዳው ይለመልማል እባቡንና ጊንጡን በእርሱ እሳት ይበላል:: በከተማና በገጠር ያለው ገዥ መንፈስ ግዛቱን ለቆ ይሄዳል::

ሥራ ከመጀመራችን በፊት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከመንቀሳቀሳችን በፊት ብርሃን የሆነው እግዚአብሔርን ቀና ብለን ብናይ አእምሮአችን በብርሃን ይሞላል:: በብርሃን የተሞላ እውቀት

ይኖረናል በሰው አእምሮ የተቀመጠው የጨለማው ዓለም እውቀት በእኛ አእምሮ ባለው እውቀትና ብርሃን የጨለመው አስተሳሰባቸው በሰማያዊ ብርሃን እንተካዋለን::

በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ያሉ ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔር ልጆች ከሁሉም አስቀድመው ጉልበታቸውን ለፀሎት ያንበረክካሉ የህይወት እንጀራ የሆነው ቃሉን ገልጠው ያነባሉ ያሰላስላሉ እነደ ቃሉ ለመኖር ራሳቸውን ሁሉን ለሚችው ጌታ አሳልፈው ይሰጣሉ:: ከብርሃን የተሰራ ሰማያዊ ቅጥር ይከተላቸዋል:: ይህ ቅጥር ሰይጣን ዲያብሎስ ቀና ብሎ የማይመለከተው ቅጥር ነው::

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በዚያን ጊዜ ምድር ቅርጽ የሌለባትና ባዶ ነበረች ጨለማም በጥልቁ ውቅያኖስ ላይ ነበረ::

እንግዲህ ሌሊቱ ነግቶአል ጨለማው አልፎአል የዓለም ብርሃን ከሆነው ጌታ ጋር በመታረቅ የብረሃን ሥራ እየሰራህ በብርሃን እንድትመላለስ ተጋብዘሃል:: ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ እኔን የሚከተል ሁሉ የሕይወት ብርሃን ያገኛል በጨለማም አይመላለስም ዩሐ.8፥12 ጨለማ የተፈጠረው ዓለም በተፈጠረችበት ጊዜ ነው ::

ማለት ሰማይና ምድር በተፈጠሩበት ዕለት ነው:: ጨለማ የመጣው ሰማይና ምድርን ተገን በማድረግ ነው:: ብርሃን ግን በትዕዛዝ ነው የመጣው እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ:: ብርሃንም ሆነ ወንድሜና እህቴ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን ብሎአል በሕይወትህ ያለው ጨለማ አልወደደውም ብርሃንም ከጨለማ ጋር አንድነት ከክርስቶስ ጋር ምን ግንኙነት አለው ከጨለማው ዓለም ክፉ ሥራ ውጣ መንፈስ ቅዱስ ሀይል ይሰጥሃል::

አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስ ያበራልሃል:: ጌታ ኢየሱስ /ዒሳ/አምኖ ዳግም ያልተወለደ ሁሉ በሕይወቱ ጨለማ አለ ሰዎች ወንጀልን ለማስራት ጨለማን ይመርጣሉ ምክንያቱም ክፉ

ስራቸው በብርሃን እንዳይገጥ ነው። በጨለማ ምን አለ ለሚለው ጥያቄ በጨለማ ያለ ነገር ስለማይታይ መዘርዘር አይቻልም በጥቅሉ ሞት አለ።

ወደተነሳንበት አቢይ ርእስ እንመለስ እስልምና እውነተኛውን የሥላሴ ትምህርት ይቃወማል ብለን አናስብም የእስልምና ምሁራን ስለ ሥላሴ አስተምህሮ በአንደበታቸው መስክረዋል በእጆቻቸው ጽፈዋል። አብድል ጣሀር የተባሉ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር እንዲህ ብለዋል። ወንጌል ለደቀመዛሙርቱ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው የሚል ትዕዛዝ ነው የተሰጣቸው። አብድል ጣሀር በመቀጠል ለክርስቲያኖች ትምህርት የጀርባ አጥንት ወንጌል፣የሐዋርያት ሥራ፣እና የጳውሎስ መልእክቶች መሆኑ ግልፅ ነው።

እነዚህ መጽሐፎች እግዚአብሔር አንድ ነው። ስሙም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው። ብለው ይላሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልዩ ስሙ የማንነቱ መገለጫ ነው።

የእኔ እውቀት ይህን ያህል ነው ። ከዚህ የበለጠ በዚህ ርእስ መወያየትና ማወቅ እፈልጋለሁ ብለዋል። የሥላሴ ትምህርት ትክክል ባልሆነ መንገድ የተረዳው ሙስሊም ህብረተሰብ በጊዜው ወደ እነርሱ የደረሰው ትክክለኛውን የሥላሴ ትምህርት ሳይሆን አብ ወልድ ማርያም የሚለው መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ከእነርሱ በኋላ ለተነሣው ትውልድ ይህንኑ ነው ያስተላለፉለት። የሚታረም ስህተት ስለሆነ ወደፊት ውጤቱን እንጠብቃለን።

ቅዱስ አውግስቲን እና ካልቪን ታላቅ የሆነ ምስጢር አለን ይህም የሥላሴ አስተምህሮ ነው ብለዋል። ስለሆነም አንድ ነገር እርግጠኞች ነን። የሥላሴ ትምህርት ከሰው የመጣ ትምህርት አይደለም። ሚስጥሩ ግን በሕይወት ያለ እና ሕይወት የሚስጢር

ነው አስተምህሮው የበለፀገ እና ውብ የሆነ ሚስጥር አለን በሌላ አገላለፅ የሰው አእምሮ ያመነጨው ከብዙ ሰዎች አስተሳሰብ ተጨምቆ የመጣ ውጤት አይደለም። ነገር ግን እምነቱ የተመሰረተው በእውነት ላይ ነው።

በቁርዓን የተገለጠው የሥላሴ ትምህርት የክርስትያኖችን አስተምሕሮ አይደለም። የሥላሴ ትምህርት ክርስቶስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ይህ አስተምሮ እንዲቀጥል ማድረግ የኛ ሀላፊነት ነው። ከሐዋርያት ዘመን እስከ ሁለተኛ ክፍለ ዘመን ለክርስትና እምነት አንድ ወጥ የሆነ መመሪያ አልነበረውም እምነታቸው እንደ ተጻፈው እንደ ቃሉ እየተገበሩ ይኖሩ ነበር። የስህተት ትምህርት በመከሰቱ ሐዋርያት ላስተላለፉት የተለየ እንግዳ ትምህርት የጳውሎስ የጴጥሮስ የዩሐንስ ኮቴ ያልተከተለ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለያዩ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ፈጣን ውሳኔ ማስተላለፍ ነበረባት በተለይም የአርዮስ ትምህርት ወደ ቤቴክርስቲያን እንዳይገባ ረድቶአል። የእርሱ አገላለፅ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን የገለፀበት ነው እንጂ ሥላሴን አይገልፅም የሚል ነው።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ከተገለጠውና ከሚገለጠው የስህተት ትምህርት ተጠብቃ የሕይወት ቃል የምሥራቹን እያወጀች እስከ ምፅዓቱ ቀን ነቅታ የተሰጣትን ተልኮ እየተወጣች መጠበቅ አለባት።ኢየሱስ ወደ እነርሱ ቀረበና እንዲህ አላቸው ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ በአብና በወልድ መንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀመዝሙር አድርጉአቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈፅሙ አስተምሩአቸው እነሆ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። ማቴ. 28፥18

በአጠቃላይ ሥላሴ በቁርዓን በሚለው ርእስ የተመለከትነው ክርስቲያኖችን የማይመለከት መሆኑ በክርስትና የተወገዘ መሆኑ

እግዚአብሔር ኢየሱስ ማርያም የሚል የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑ እና በጊዜው ተነስተው የነበሩ ብዙ አማልእክት የሚያመልኩ ያመጡት እንደሆነ ግንዛቤ እንዳገኛችሁ ተስፋ አደርጋለሁ::

## ሰ. ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ

ሰው ከምድር የተሰራ ምድራዊ ነው:: ደግሞ በውስጡ ካለው የሕይወት መንፈስ የተነሣ ሰማያዊ ነው:: እግዚአብሔር አምላክ /ያህዌ ኤሎሂም/ ከምድር ዓፈር ወስዶ ሰውን አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ ዘፍ. 2፥7 ሰው በጊዜ በቦታ መረዳትና በማገናዘብ አቅሙ የተወሰነ በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር ያለው መረዳት ውስን ነው:: በተለይም የሥላሴ ሚስጥር የሚታየው ዓለም ማለት ተፈጥሮአዊ ሰው ጌታን የማያውቅ በሰዋዊ ትንታኔ መረዳት ያዳግት ይሆናል::

ሚሥጥሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው:: የተገለጠው ግን የዚህን ህግ ቃሎች ሁሉ እንድናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለም ለልጆቻችን ነው:: ዘዳ. 29፥29

### 1. *እግዚአብሔር ራሱን እንዲህ ገልጧል::*

ሀ. እግዚአብሔር አብ አባታችን ነው:: 2 ተሰሎንቄ 2፥16 "ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደደን በጸጋውም የዘላለም መፅናናትን መልካም ተስፋንም የሰጠን አባታችን እግዚአብሔር::

ለ. እግዚአብሔር ወልድ /ዒሳ/ ነቢያቶች አምላክ ብለው ጠርተውታል:: ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል:: ስሙም ድንቅ መካሪ ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም ልዑል ይባላል:: ኢሳ. 9፥6

ሐ. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ተብሎአል ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬት ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ልብህን

ስለ ምን ሞላው የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም ሐዋ. 5፡3-4

2. ጌታ በሚለው ቃል ተጠርተዋል

ሀ. እግዚአብሔር አብ ጌታ ነው ሉቃ. 10፥21 "በዚያንስ ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት አደረገና የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ ይህንን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለህፃናት ስለ ገለጥክላቸው አመሰግናለሁ እዎን አባት ሆይ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኗአል"።

ለ. እግዚአብሔር ወልድ /ዒሳ/ ጌታ ነው ሐዋ.10፥36 እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የላከው የሰላም ወንጌል መልእክት ይኸው ነው።

ሐ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጌታ ነው ። የጌታ መንፈስ ባለበት ነፃነት አለ 2ቆሮ.3፡17

3. <u>ዘላለማዊ የሚለው ቃል የዘመንን ርዝማኔ ለማመልከት ነው።</u>

ሀ. እግዚአብሔር አብ ዘላለማዊ ነው። ዳንኤል 6፥26 በመንግስቴ የሚኖር ሕዝብ ሁሉ የዳንኤልን አምላክ እንዲፈራና እንዲያከብር በአዋጅ አዝዣለሁ እርሱ ህያውና ዘላለማዊ አምላክ ነው እርሱ ዘላለማዊ ንጉሥ ነው። ለመንግስቱም ፍፃሜ የለውም።

ለ. እግዚአብሔር ወልድ ዘላለማዊ ነው። ራዕ. 1፥8 ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል።

ሐ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው። በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ

ህልናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነፃ ይሆን? ዕብ. 9፥14

4. **በሁሉም ቦታ ይገኛል።**

ሀ. እግዚአብሔር አብ ኤፌ. 4፥6 ከሁሉም በላይ የሆነ በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለን።

ለ. እግዚአብሔር ወልድ /ኢሳ/ በሁሉም ቦታ ይገኛል። ደግሞም እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር ላይ ማናቸውንም ነገር ስለመለመን በጸሎት ቢተባበሩ በሰማይ ያለው አባቴ ይፈፅምላቸዋል። ምክንያቱም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ስፍራ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ። ማቴ. 18፥19-20

ሐ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ቦታ ይገኛል። መዝ. 139፥7-10 ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ወደ ሰማይ ቢወጣ አንተ በዚያ አለህ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ በንጋት ክንፍ ተነስቼ ብበር እስከ ባህር ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ በዚያ ቢሆን እጅህ ትመራኛ ለች ቀኝህም አጥብቃ ትይዘኛለች።

5. **አምልኮ ተቀብለዋል። ዮሐ 4፥23**

ሀ. አብ አምልኮ ተቀብሎአል በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል እንዲያውም አሁን መጥቶአል እግዚአብሔር አብም የሚፈልገው እንደዚህ የሚሰግዱለትን ነው።

ለ. ወልድ አምልኮ ተቀብሎአል ፊልጵስዩስ 2፥10-11 ይኸውም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ቅልበቅ ሁሉ ለኢየሱስ ስም

ይንከረከክ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይምሰክር ዘንድ ነው።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና ሮሜ8፥27

## 6. ፍቅር የእግዚአብሔር የማንነት ባህርይ

ሀ. እግዚአብሔር ዮሐ.16፥27 ምክንያቱም አብ ራሱ ስለሚወዳችሁ እኔን ስለወደዳችሁኝና ከእግዚአብሔር እንደመጣሁ ስላመናችሁ ነው በዚህ ጥቅስ መሰረት አብ ደስ የሚሰኘውና ሰዎችን የሚወደው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያምኑ አምነውም ሲቀበሉ ነው።

ለ. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. 15፥15 አገልጋይ ጌታው የሚያደርገውን ስለማያውቅ ከእንግዲህ ወዲህ አገልጋዮች አልላችሁም ነገር ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጥሁላችሁ ወዳጆቼ ብያችኋለሁ።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ 2ጢሞቴዎስ 1፥7 ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠን የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ ነው። የፍርሃት መንፈስ አይደለም ።

## 7. ቅድስና

ሀ. እግዚአብሔር አብ ዮሐንስ ወንጌል 17፥11

እኔ ከእንግዲህ ወዲህ በዓለም ላይ አልኖርም እነርሱ ግን በዓለም ናቸው። እኔ ወደ አንተ መምጣቴ ነው ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህ የሰጠኸኝን ጠብቃቸው።

ለ. እግዚአብሔር ወልድ ሉቃ. 1፥35

መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል። የልዑል እግዚአብሔር መንፈስ በአንቺ ላይ ይሆናል።

ስለዚህ ከእንቺ የሚወለደው ሕፃን ቅዱስ የእግዚአብሔርም ልጅ ይባላል::

ሐ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኤፌ. 4፥30 ለምትዋጁበት ቀን መያዣ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ::

## 2. የእግዚአብሔር አንድነት

እግዚአብሔር አንድ ነው አንድ አምላክ አለን እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ በፍፁም ነፍስህ በፍፁም ሀይልህ ውደድ ዘዳ. 6፥4

ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ ዘፀ. 20፥3 አንተም እንደ ሌላው ሕዝብ ጣዖትን አትከተል ከንቱ በሆኑ ጣዖቶች ላይ የሚንጠላጠሉ ሊያገኙ የሚገባቸውን ጸጋ ያጣሉ::

## 3. የእግዚአብሔር ሦስትነት

እግዚአብሔር በአሮጌው ኪዳን የሚታወቀው በአጠቃላይ በአንድነቱ ነው:: የህልውናው ሦስትነት የተገለፀው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም ከመጣ በኋላ ነው:: ቢሆንም በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር የተጠቀሰባቸው በርከት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ::

### ምሳሌ በብሉይ ኪዳን እንዲህ ተገልጿል::

1. ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር ዘፍ. 1፥26»
2. ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ «እነሆ አዳም ደጉንና ክፉውን ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት በማግኘቱ ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖአል:: ከእንግዲህ ወዲህ እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ወስዶ በመብላት ለዘላለም መኖር አይገባውም አለ» ዘፍ. 3፥22

3. ስለዚህ ኑ እንውረድ እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውንም እንደባልቀው:: ዘፍ. 11፥7
4. ወደ እኔ ቅረቡ ይህንም ስሙ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርኩም ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ አሁንም ጌታ እግዚአብሔር እና መንፈሱ ልከውኛል ኢሳ. 48፥16

እኔ የሚለው ኢሳይያስ ሳይሆን ከመለኮት አንዱ እንደ ሆነ እንረዳለን ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ስል ደግሞ ሁለቱ የመለኮት አካላት አብና መንፈስ ቅዱስን ማለቱ ነው:: ከዚሁ ከኢሳያስ 48 ሳንወጣ በቁጥር አስራ ሁለት እኔ እኔው ነኝ ፊተኛው እኔ ነኝ ይህን ያለው ክርስቶስ ራሱ ነው::

እኔ የሚለው በአዲስ ኪዳን ብዙ ቦታ ተጠቅሷል:: ባየሁት ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ በእግሩ ስር ወደቅሁ እርሱም ቀኝ እጁን በላየ ጭኖ እንዲህ አለኝ አትፍራ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ::ራዕ.1፥17 ይህ ጥቅስ ትልቅ መልእክት አለው እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን በጌታ በኢየሱስ ያመንን በፀሎት በእግሩ ስር ስንወድቅ የጌታ ቀኝ እጁ ወደ እኛ ትዘረጋለች በዚህ ጊዜ የምንሰማው ድምፅ ሁሉን ነገር አስረስቶ ሰላም ደስታ ተስፋ የሕይወት መታደስ የሚያመጣ ነው:: ይኸውም እኔ ነኝ አትፍራ የሚለው ድምፅ ነው:: የሚንጓዘው የሕይወት መንገድ ግራ ሲገባን ማዕበሉ ሲበረታ በማበሉ ላይ ቆሞ ማዕበሉን በመገሰፅ እኔ ነኝ የሚል አምላክ አለን::

ደቀመዛሙርቱም በባሕሩ ላይ እየተራመደ ሲሄድ ባዩት ጊዜ በጣም ፈርተው ደነገጡ «ይህ ምትሐት ነው!» ብለውም በፍርሀት ጮኹ:: ማቴ. 14፥26-27

5. ጌታ ኢየሱስ ስጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶአል:: እግዚአብሔር አብ ደግሞ ከሰማያት ሆኖ ድምፁን አሰምቶአል:: ኢየሱስ ተጠምቆ ከውሀ እንደ ወጣ ወዲያውኑ ሰማይ ተከፈተ

የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ሲያርፍ አየ። በዚያኑ ጊዜ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።ማቴ. 14፥16-17

6. እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀመዝሙር አድርጉአቸው። ማቴ. 28፥19

7. ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት መልእቱን የዘጋው እንዲህ ነው።

በወድማማች ስሜት እየተሳሳማችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።2ቆሮ.13፥12-14

ከመልእክቱ መዝጊያ ምንድነ ነው የሚንማረው እግዚአብሔር እንዲሁ ወድዶናል። እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለ ወደደ አንድ ልጁን ሰጠ። ስለዚህ በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም። ዮሐ. 3፥16

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋውን ሰጥቶአናል። ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በእኛ አደረ ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ዩሐ. 1፥14 መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንድናደርግ ያግዘናል። እንደዚሁም ከአማኞች ጋር ህብረት እንድናደርግ ይረዳናል።

በዚህ ዘመን እርስ በርስ መቆሳሰል እየበዛ ስለመጣ ብዙዎች ከህብረት እየራቁ ነው። ከክርስቲያኖች ጋር የሚኖረን ሕብረት በምንም አይተካም እርስ በእርስ በመሸካከም ያለፈውን ቁስል በመርሳት ህብረታችን ማደስ አለብን።

እኛ ሁላችን ከአንድ መንፈስ ጠጥተናል።ምክንያቱም አይሁዳውያንም ብንሆን ነፃ ሰዎች ብንሆን አንድ አካል ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀናል። 1ቆሮ 12፥13

ስለ ሥላሴ ምስጢር ሦስትነትና አንድነት በመጠኑ የሚገልፁ ምሳሌአዊ አገላለጾች አሉ።

ዛፍ፡- የዛፉ ሥር ግንድ ቅርንጫፍ

ፀሀይ፡- የፀሀይ አካል ብርሀን ሙቀት

ውሃ፡- ፈሳሽ እንፋሎት በረዶ

እነዚህ ምሳሌዎች ስለ ሥላሴ ምስጢር ለመረዳት መጠነኛ ፍንጭ የሚሰጡ ቢሆኑም የእግዚአብሔርን ማንነት ሊገልፁ አይችሉም እግዚአብሔርን በየትኛውም ምሳሌ መመሰል ትክክል አይደለም።

እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ ኢሳ. 40፥18

## የትምህርተ ሥላሴ መግለጫ

አንድ የማይነጣጠል የማይከፋፈል አምላክ አለ እግዚአብሔር በቁጥር በባህሪ አንድ ነው። በዚህ አንድ አምላክ ሦስት አካል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉ። አካል የሚለው ቃል የሥላሴን ትምህርት በደንብ መግለፅ አይችልም። ምክንያቱም አካል/person/ ቃሉ ራሱ ለሰዎች ስንጠቀም የተለያዩና አንድ ያልሆኑ ሰዎች ስለሚያመለክት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በሦስት አካል እርስ በርሳቸው የተለያዩና ለየብቻ የሆኑ ሳይሆን በዚህ በሦስት አካል እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው ። እግዚአብሔር ያልተካፈለና ያልተቀነሰ እርሱነቱ በሙላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እኩል ናቸው። እኩል ስለሆኑ አንደኛው ከሌላው ሊበልጥ ወይም ሊያንስ አይችልም። ስለሆነም እኩል ክብር አላቸው አብ ዓለምን እንዲሁ ወድዶ አንድያ ልጁን ሰጠን ወልድ መልካም እረኛ በመሆን ነፍሱን

ለበጉቹ አሳልፎ ሰጠ ዩሐ. 10፥11መንፈስ ቅዱስ ሰዎች በኃጢአታቸው ተጸጽተው ወደ ወልድና አብ እንዲመለሱ ሰዎችን በመውቀስ ዳግመኛ እንዲወለዱ ያደርጋል። ዩሐ. 16፥8 ቲቶ.3፥5

እንግዲህ የሥላሴ አስተምህሮ ግልጠት እግዚአብሔር ለሰው የመገለጡ ውጤት ነው። መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው ዮሐ. 1፥18 የሥላሴ ማንነት ከብሉይ ኪዳን ዘመን በተሻለ በሰፊው በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ገልጦታል።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር በእኛ የማስታረቅ ቃል አኖረ። 2ቆሮ. 5፥19

## VI. ወንጌል እውነት መሆኑን እንዴት አውቃለሁ

የሰው ህይወት በፍለጋ የተሞላ ነው። የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት የምንላቸው ምግብ ልብስ መጠለያ ናቸው። አራተኛው የሰው መሰረታዊ ፍላጎት መንፈሳዊ መብል ነው። ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ። ሦስቱን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት መንግሥታት ይወያያሉ ምክራቸውንም በፊርማቸው ያጸድቃሉ። አራተኛው የሰዎች መሰረታዊ ፍላጎት ግን በብዙዎች ዘንድ ተረስቶአል ወይም መስመሩን በሳተ መንገድ ለይሕወት የማይስማማ መንፈሳዊ የመሰለ ግን መንፈሳዊ ያልሆነ የሚመገቡ ከቁጥር በላይ ናቸው።

የመንፈሳዊ ረሀብ ባዶነት ለመሙላት ሰዎች ሀይማኖቶኞች ይሆናሉ። እውነተኛው ሀይማኖት እንዴት ማወቅ እችላለሁ ወይም እንችላለን? ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ አለው። የሐዋሪያው ጳውሎስ መልእክት 1ተሰ. 5፥21 "ሁሉንም ፈትኑ መልካሙን ያዙ" ። መልካም ማን ነው? መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ሕይወቱን

ስለ በጐቹ አሳልፎ ይሰጣል:: ዮሐ. 10፥11 ምርጫችን ይህ ጌታ መሆን አለበት::

ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስ መልካም እና ትክክለኛ ነው ይላል::የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ በተወረደው ወደናንተምበተወረደው አመንን አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን::ሱራ 29፥46

የመጽሐፉ ሰዎች የሚላቸው ክርስቲያኖችን ነው::በወንድማማች መንፈስ ስለ ወንጌል እውነተኝነት ከቁርዓንና ከኢንጁል /ወንጌል/ እያመሳከርን እርስ በእርስ መማማር አለብን:: ቁርዓን ወንጌል ትክክለኛ ነው የእኛ የእናንተ አምላክ አንድ ነው እኛ ለእናንተ አምላክ ታዛዦች ነን ብሎአል:: የእኛ አምላክ የሰጠን የፍቅር ትእዛዝ አለ:: ይኸውም ብሩህ ደመና ጋረዳቸው ከደመናውም ውስጥ በእርሱ ደስየሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ:: ማቴ. 17፥5 የአላህ ፈቃድ ሰዎች ሁሉ ዒሳን እንዲሰሙት ነው::

እነርሱ ዘንድ ተውራት እያላቸው በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለበት ስትሆን እንዴት ያስፈርዱሃል::ከዚያም ከዚህ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ እነዚያም በፍጹም ምእናን አይደሉም::ሱራ 5፥43 የእስራኤልንም ልጆች ምስጉንን ስፍራ በእርግጥ አሰፈርናቸው ከመልካም ሲሳዮችም ሰጠናቸው ዕውቀትም /ቁርዓን/ እስከ መጣቸው ድረስ አልተለያዩም ጌታህ በርሱ ይለያዩበት በነበሩበት ነገር በትንሳኤ ቀን በመካከላቸው ይፈርዳል:: ሱራ 10፥93

እኛ የትንሳኤ ቀን እንዳለ «እናምናለን ሙስሊሞችም ያምናሉ የፍርድ ቀን እንዳለ ያምናሉ እኛም እናምናለን ተመሳሳይ አስተምህሮ አለን:: የሚከተለውን ጥቅስ ልብ ይበሉ:: በነርሱም ላይ

በውስጧ ነፍስ በነፍስ ዓይንም በዓይን አፍንጫ በአንፍጫ ጆሮ በጆሮ ጥርስ በጥርስ /ይያዛል/ ቁስሎችንም ማመሳሰል አለባቸው በማለት ጻፍን በርሱም የመጸወተ ወይም የማረ ሰው ለርሱ /ለሠራው ኃጢያት/ማስተሰሪያ ነው:: አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው:: ሱራ 5፡45

እነዚህ ጥቅሶች ከብሉይ ኪዳን ሀሳብ ጋር አንድ ናቸው በዓይን ምትክ ዓይን በጥርስ ምትክ ጥርስ በእጅ ምትክ እጅ በእግር ምትክ እግር በቃጠሎ ምትክ ቃጠሎ በቁስል ምትክ ቁስል በመፈንከት ምትክ መፈንከት በሚለው ህግ መሰረት ይወሰን :: ዘፀ. 21፡24-25 የሌላውን ሰው አጥንት የሰበረ አጥንቱ ይሰበር የሌላውን ሰው ዓይን ቢያወጣ ዓይኑ ይውጣ ጥርስም ቢሰብር ጥርሱ ይሰበር በሌላው ሰው ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ቢያደርስ የዚያው ዓይነት ጉዳት በእነርሱ ላይ ይመለስበት:: ዘሌ. 24፡20 በሱራ 5፡45 ከላይ የቁርዓን ክፍል ቀጥታ ከዚሁ ካነበብነው የብሉይ ኪዳን ሀሳብ የተወሰደ ነው:: ምክንያቱም ሙስሊሞች በታውራት በዘቡርና በኢንጂል ስለ ሚያምኑ ነው::

ወደ አንተ መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አውረድን በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል:: ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድ አደረግን አላህም በሻ ኖሮ አንድ ህዝብ ባደረጋችሁ ነበር ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ /ለያያችሁ/ በጐ ሥራዎችንም /ለመሥራት/ ተሽቀዳደሙ መመለሳችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው በርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል:: ሱራ 5፡48

ጌታ ስለ ህግ ምንድን ነው ያለው እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር

አልመጣሁም እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት ጭረት ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስከፈፀም ድረስ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉም ካነሱት ትዕዛዛት አንዲቱን ለሚሽር ለሰውም እንዲሁ ማንም ሰው በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል:: የሚያደርግ ግን የሚያስተምር ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል:: ማቴ. 5፥17-19

ብዙዎች የማስተማር አገልግሎታቸውን በጥሩ ሁኔታ ይወጣሉ:: ከማስተማር ቀጥሎ ያለው በሕይወት የመተግበር እና እንደቃሉ የመኖር ሀላፊነት ይዘነጋሉ:: ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጽሐፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደቅዱስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሳት የተነሣ በሀይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠው ስለ ልጁ ነው:: እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በእርሱ ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ የኢየሰሱ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ ሮሜ. 1፥1-6

ወንጌል ከጥሪ ይጀምራል:: ጳውሎስ የመጀመሪያ ስሙ ሳውል ነበር የጌታን ደቀመዛሙርቱ ለመግደል እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናቱ በመሄድ የጌታ የኢየሱስ መንገድ የሚከተሉ ወንዶችና ሴቶች ቢያገኝ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት የሚያስችል ደብዳቤ እንዲሰጠው ሊቀካህናቱን ጠይቆ ባገኘው ፈቃድ ጉዞ ወደ ደማስቆ ጀመረ:: ጳውሎስ ድንበር ዘለል አሳዳጅ ነበር:: ደማስቆ የሶሪያ ዋና ከተማ ነበረች በሰው ሀገር ሂዶ ለማሳደድ መነሳቱ በጥላቻ የተሞላ በመግረፍና በማሰር የወንጌል እውነት ለመከልከል የተነሣ ሰው ነበር::

ሲሄድ ወደ ደማስቆ በደረሰ ጊዜ በዙሪያው ድንገት ከሰማይ ብርሃን አንፀባረቀበት በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ወደቀ ሳኦል ሳኦል

ለምን ታሳድደኛለህ የሚል ድምፅ ሰማ ሶአል አንተ ማን ነህ ብሎ ጠየቀ የጌታ መልስ ሳኦል ያልጠበቀው ነው:: አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ /ዒሳ ነኝ/ ሳኦል ከወደቀበት ተነስቶ ዓይኑን ለመግለጥ ቢሞክርም ማየት አልቻለም:: የእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ ወሰዱት ሦስት ቀን ሙሉ ምንም ሳይበላ ሳይጠጣ በድንጋጤ እንድሁ ቆየ::

ጌታ ለሐናንያ ሳኦል ባለበት ቤት ሄዶ እንዲፀልይለት በራዕይ ተናገረው ሃናንያ በኢየሩሳሌም ባሉ ቅዱሳን ብዙ ክፉ ነገር ማድረጉን ሰምቻለሁ ከዚህም ስምህን የሚጠሩትን ለማሰር ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብሎአል:: ሳኦል የጌታ ኢየሱስን ተከታዮች የሚያሳድድ መሆኑ በመካከለኛው ምስራቅ ያለው ሕዝብ ሁሉ ያውቃል ማለት ነው ከሃናንያ መልስ እንደ ምንረዳው::

ጌታም ሐናንያን እንዲህ አለው እርሱ ስሜ ለአረማውያን ለእስራኤላውያን ሰዎች የሚያሳውቅ የእኔ ምርጥ አገልጋይ ስለሆነ ወደ እርሱ ሂድ አለው:: አረማውያን ማለት ጣዖት አምላኪዎች እግዚአብሔርን የማያውቁ ማለት ነው::

ሐናንያ እጁን በሳኦል ጭኖ ወንድሜ ሳኦል ወደዚህ ስትመጣ ሳለህ በመንገድ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ እንደገና ማየት እንድትችልና መንፈስ ቅዱስ እንድሞላህ ልኮኛል አለው:: ወዲያውም ማየት ቻለ ተነስቶ ተጠመቀ መብል በላና በረታ በደማስቆ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው እያለ በየምኩራብ ማስተማር ጀመረ ሐዋ. 9፥1-20

## ሳኦል የወንጌልን እውነተኝነት እንዴት አረጋገጠ ?

1. ጌታ በብርሃን ተገለጠለት ብርሃኑ የወደቀው በቀጥታ በዓይኑ ላይ ነው:: በክረምት ወራት ልብ ብላችሁ ከሆነ የመብረቅ ድምፅ ከመስማታችን በፊት በድንገት በፍጥነት የሚወረወር ጨረር

በዓይናችን ላይ በሚያርፍበት ጊዜ ቶሎ ብለን ዓይናችንን እንጨፍናለን ከጨረሩ የብርሃን ሀይል የተነሣ እንስሳት እንኳ ይደነብራሉ:: ከጌታ ዘንድ የወጣው ብርሃን የጳውሎስን የተፈጥሮ ዓይን አሳወረው :: የዓይኑ ብርሃን ያጣው ጳውሎስ በሰው እየተመራ ወደ ከተማ ገባ ሰዎች የወንጌልን እውነት እንድያውቁ ጌታ ወደ እውነት የሚመራው ብርሃኑን ማብራት አለበት::

ጨለማ የእውነትን መንገድ ይጋርዳል:: ብርሃን ግን የእውነትን መንገድ ያሳውቃል:: ጨለማ እውነትን ከሰው ይሰውራል ብርሃን እውነትን ይገልጣል ጨለማ እርምጃን አሰናክሎ ጉድጓድ ውስጥ ይጥላል ብርሃን ግን አካሄድን ከመሰናከል አውጥቶ ትክክለኛ ውን አቅጣጫ ያሳያል::

ከቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት አይደለምን? ከዚህ ዓለም ብርሃን የተነሣ ስለሚያይ በቀን የሚመላለስ አይሰናከልም የሚሰናከለው ግን በሌሊት የሚመላለስ ነው ብርሃን የለውምና:: ዮሐንስ ወንጌል 11፥9

አንተ የሚትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሀል እያልን ማወጅ አለብን ሰዎች የወንጌልን እውነት እንድያውቁ ከእኛ ዘንድ ያለው ብርሃን ሊያበራላቸው የግድ ነው::

2. ለምን ታሳድደኛለህ የሚለውን የጌታ ድምፅ ሰማ:: ጳውሎስ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኝ መስሎት ሳያውቀው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያሳድድ ነበር የሚሰራው ሥራ ትክክል መሆኑን አለመሆኑን አያውቅም ምክንያቱም የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችን ፈቃድ ጠየቀ እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አልጠየቀም::

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ይፈልጋሉ ከዚህ የተነሣ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይሄዳሉ አንድ ሰው ወደ ጠንቋይ ቤት ሂዶ አስጠንቁሎ ከተመለሰ በኋላ በጠንቋይ በኩል የተነገረው ቃል ሰይጣን ተናገረኝ አይልም ለሌላው ሰው እግዚአብሔር ተናገረኝ ብሎ ነው የሚናገረው::

አይመስለኝም የአይሁድ የሀይማኖት መሪዎች ካሉት የበለጠ ማለት ይችላሉ ግን አላደረጉትም ፡፡

ስለ ዒሳ ከተለያዩ ሰዎች የሰማኸው እኔ ካነሳሁት ሀሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ከዚያ የተሻለ መንገድ በሰዎች በስሚ ስሚ ከመስማት ይልቅ ኢንጂልን ብታነብ ከተለያዩ ሐይማኖታዊ ድርጅቶች ከሰማኸው የተሻለ ከመጽሐፉ ባለቤቶች ራሱን መጽሐፉን ስለ አገኘህ ስለ ዒሳ የሚኖርህ እውቀት የተቀነጨበ ሳይሆን ሙሉ እውቀት ይኖርሀል ማለት ነው::

ጴጥሮስም መልሶ አንተ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መለሰ:: ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም እኔም እንዲህ እልሀለሁ ጴጥሮስ አንተ አለት ነህ በዚህችም የመሰረት ድንጋይ ላይ ቤተክርስቲያኔን እመሰርታለሁ ይህችንም ቤተክርስቲያን የሞት ሀይል አንኳ አያሸንፋትም እነሆ ለአንተ የመንግስተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሀለሁ በምድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል:: ማቴ. 16፥13-19

በዚህ ጥቅስ መሠረት ዒሳ ነቢይ ነው የሚለው የአይሁድ ግምታዊ መልስ ትክክል እንዳልሆኑ አስረግጦ ተናግሮአል እንዲህ በማለት የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ የተባረክህ ነህ ምክንያቱም ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ ነው እንጂ ሰው አይደለም የጴጥሮስ መልስ ግምታዊ ሳይሆን ራሱን ዒሳን ያስደነቀ ከብዙ ሰዎች የተሰወረ መገለጥ ተናገረ ወንጌል እውነት መሆኑ ለማወቅ መገለጥ አስፈላጊ ነው::

እነዚህ ጥቅሶች የጴጥሮስ መገለጥ የሚያረጋግጡ ናቸው:: እነርሱም ስለ ምን ፈለጋችሁን በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ

አላወቃችሁምን? ሉቃ. 2፥49 አባቴ እስከ ዛሬ ይሰራል እኔም ደግሞ እሰራለሁ ብሎ መለሰላቸው ዩሐ. 5፥17

እኔ የአባቴን ሥራ የማልሰራ ከሆንሁ አተመኑኝ የአባቴን ሥራ የምሠራ ከሆንሁ ግን በእኔ እንኳ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ በዚህ ዓይነት አብ በእኔ እንደሆነ እና እኔም በአብ እንደሆነ በሚገባ ታውቃላችሁ ዮሐ. 10፥37-38

እንግዲህ የሰማያዊ ጥሪ ተከፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የእምነታችን ሐዋርያና ሊቀካህናት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስቡት ... ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ እንደ አንድ ታማኝ ሎሌ ነው:: እኛም የምንተማመንበትና የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን ብንይዝ ቤቱ ነን:: ዕብ. 3፥1-6

እስከ አሁን የተመለከትነው የወንጌል እውነት እንዴት አውቃለሁ በሚለው ርዕስ ቁርዓን መልካምና ትክክል ነው ብሎ መመስከሩ ቁርዓን ወንጌልን ለመደገፍ እንጂ ለመቃወም እንዳልመጣ አይተናል መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርዓን በማመሳከር ለማንበብና እውነትን ለማወቅ መንገድ ይከፍታል::

## VII. መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ተበርዟል?

### ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን ምን ይላል

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል አይደለም ተበርዟል በፊት በነበረው ቃሉ ላይ ሰዎች የራሳቸው ሀሳብ ጨምረውበታል ይላሉ እውነት መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል? መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሀገሮች ቋንቋዎች ተተርጉሙአል ጥንታዊያን የሆነ ቅጂዎች በተለያዩ ሀገሮች አብያተክርስቲያናት ይገኛሉ:: በተጨማሪም በተለያዩ ዘመናት በስነምድር ተመራማሪዎች ፍለጋ የተገኙ ጥንታዊ ቅዱሳት መጽሐፍት አሁን በእጃችን ካለው መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ልዩነት የላቸውም ታላቁ መጽሐፍ በሁለት ይከፈላል የብሉይ ኪዳንና የአዲስ

ኪዳን መጽሐፍ ይባላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው የተፃፈው::

ይህንንም በይበልጥ የሚያረጋግጥል የነቢያት ቃል አለን ይህን ቃል ሌሊቱ እስኪነጋና የንጋት ኮከብ በልባችሁ እስኪበራ ድረስ በጨለማ እንደሚበራ መብራት አድርጋችሁ ብትጠነቀቁለት መልካም ነው:: ከሁሉ በፊት ማስተዋል የሚገባችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘ ውን ማንኛውንም ትንቢት ማንም ሰው በራሱ ግላዊ አስተሳሰብ ሊተረጉም አለመቻሉን ነው:: ምክንያቱም ማንኛውም ትንቢት በሰው ፈቃድ ከቶ አልመጣም ነገር ግን ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው:: 2ጴጥ. 1፥19-21

ከዚህ በኋላ ሙሴ ለሕዝብ እንዲህ አለ:: ለማስተምራችሁ ሕግና ሥርዓት ሁሉ ታዛዥዎች ሁኑ ይህንን ቢታደርጉ በሕይወት ትኖራላችሁ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁንም ምድር ትወርሳላችሁ በምሰጣችሁ ሕግ ላይ ምንም ነገር አትጨምሩ ወይም ከእርሱ ምንም ነገር አታጉድሉ እግዚአብሔር አምላካችሁ በእኔ አማካይነት ለሰጣችሁ ሕግ ታዛዥዎች ሁኑ ዘዳ. 4፥1-2

ዒሳ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊነት ሲናገር እንዲህ አለ በእውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈፀማል እንጂ በሕግ አንዲት ጭረት ወይም አንዲት ነጥብ አትሻርም ማቴ.፭፥18

እንግዲህ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ አድርጉ በእርሱ ላይ ምንም አትጨምሩ ከእርሱም አንዳች ነገር አታጉድሉ ዘዳ. 12፥32

ሰዎች በክፉ ተነሳስተው መጽሐፍ ቅዱስን እንዳይበርዙ ከፋታቸውን ሳይተገብሩ አሳህ ሐሰተኛ መሆናቸውን ይገልጣል እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ይፈፅማል የእርሱን ጠባቂነት

ለሚፈልጉ ሁሉ እንደጋሻ ነው፡፡ እርሱ ያላለውን ብሉአል ብትል ይገሥፀሀል ሐሰተኛ መሆንህንም ይገልጣል፡፡ ምሳሌ 30፥5-6

ዩሐንስ ራዕዩን ሲዘጋው እነሆ በዚህ መጽሐፍ የተፃፈውን የትንቢት ቃል የሚሰማውን ሁሉ አስጠነቅቃለሁ ማንም በዚህ ቃል ላይ አንዳች ነገር ቢጨምር በዚህ መጽሐፍ የተፃፉትን መቅሰፍቶች እግዚአብሔር ይጨምርበታል ማንም በዚህ መጽሐፍ ከተፃፉት ቃሎች አንዳች ነገር ቢያጉድል በዚህ መጽሐፍ ከተነገሩት ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ድርሻውን ያጉድልበታል የእነዚህ ነገሮች ምስክር የሆነው አዎን በቶሉ እመጣለሁ ይላል አሜን ጌታ ሆይ ና ፡፡

አንድ ሰው እንዲህ አለ ለሙስሊም ወገኖቻችን ወንጌልን በምንናገርበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል አይደለም ተበርዟል ብለው በድፍረት መልስ ይሰጡናል፡፡ እነርሱን ለማሳመን ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ጥቅሶችን አውጥተን እናስረዳችኋለን ብሉም ከቁርዓን ጥቅሶችን አውጥተን የመጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ እናሳያቸዋለን በተጨማሪ ለምን የቁርዓን መበረዝና አለመበረዝ አንስተን አንወያይም ብሉአል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በጊዜ ብዛት በሰው ሀሳብ አይተካም ዘላለማዊ ነው፡፡ ነገር ግን ለእርሱ ያለኝን ፍቅር ከቶ አይገታም ለእርሱ የሰጡሁት የተስፋ ቃል ከመፈፀም ወደ ኋላ አልልም ከእርሱ የተስፋ ቃል አንዱን እንኳን አላስቀርም መዝ, /89/33-34

ሙስሊሞች ዒሳ ዳግም ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደሚመጣ ያምናሉ ኢሳ ደግሞ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ አያልፍም ወይም አይበረዝም፡፡

በዚያን ጊዜ ከዚያ ሁሉ መከራ በኋላ ፀሐይ ትጨልማለች፡፡ ጨረቃም ብርሃንዋን አታሳይም ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ በሰማይ ያሉ ሃይሎችም ይናወጣሉ፡፡ ከዚያም በኋላ የሰው ልጅ

በታላቅ ሃይልና ክብር በደመና ሲመጣ ይታያል መላእክቱንም ይልካል እነርሱ በአራቱ አቅጣጫ ሄደው ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ የሚገኙትን ለእርሱ የተመረጡትን ሰዎች ይሰበስባሉ።

የበለስ ዛፍ ምሳሌ ትምህርት ይሁናችሁ ቅርንጫፎችዋ ሲያቆጠቁጡና ቅጠሎችዋም ሲለመልሙ ያን ጊዜ ጸደይ እንደቀረበ ታውቃላችሁ። እንዲሁም በእናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የሰው ልጅ የሚመጣበት ጊዜ መቅረቡንና በበር መቆሙን ዕወቁ በእውነት እላችኋለሁ ይህ ትውልዱ ከማለፉ በፊት ይህ ሁሉ ይፈፀማል። ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። ማር. 13፥24-31

ዒሳ በመጨረሻው ዘመን ሲመጣ ሲል በምድራችን ላይ ታላላቅ ነገሮች ይከናወናሉ ፀሃይ ብርሃን የመስጠት ሥራዋን ታቆማለች ጨረቃ እና ከዋክብት ከሰማይ ይወድቃሉ በሚወድቁበት ጊዜ በታን አይመርጡም በከተሞች በሰውና በትላልቅ ህንፃዎች ላይ ጉዳት ይደርሳል ከሁሉም የከፋው ሀያላን መንግስታት በጥንቃቄ በሚጠብቁት በንኩሌር በሌሎችም ተቀጣጣይ ነገሮች ላይ ውድቀው በሰውና በተፈጥሮ ላይ ትልቅ ጥፋት ይሆናል ከዚያም በኋላ የሰው ልጅ በታላቅ ክብርና ሀይል ይመጣል የሰው ልጅ የሚለው ዒሳን ነው። የሰው ልጅ የሚለው ስም ያገኘው ሰውን ሁሉ ለማዳን ከሰማይ ሰማያት ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በድንግል ማርያም ተፀንሶ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ የተሰጠው ስም ነው።

መላእክት ለእርሱ የተመረጡትን ሰዎች ይሰበስባሉ የሚለው መግለፅ እፈልጋለሁ ዒሳን ያመኑ የተከተሉ ከእርሱ በቀር ሌላ የመዳን መንገድ እንደሌለ የተረዱና የተቀበሉ ሰዎች ማለቱ ነው።

ስለዚህ ደህንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም ምክንያቱም እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም የለም ሐዋ. 4፥12

እርሰዎም እሺ ብለው ጌታን ቢያምኑ ከዘላለም ሞት አምልጠው የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደማይበረዝ ለዘላለም እንደሚኖር ዒሳ ተናግሯል:: ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ብሎአል::

## ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን ምን ይላል ?

ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መበረዝ አይናገርም እንድያውም መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል እንደሆነ እንዳልተቀየጠ ቁርዓን ይናገራል:: ቁርዓንን ያጠኑ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተባለው አስደቂ ነገሮችን ከቅዱስ ቁርዓን መገንዘብ ችለዋል:: የእኛ የአማኞች ትልቁ ችግር ቁርዓንን አለማወቃችን ነው :: ካለፈው ስህተታችን ተምረን ዒሳ የሰጠን ተልእኮ ለማከናወን ቁርዓንን ማንበብ አለብን::

ቅዱስ ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እንመለከት በመካከላቸው አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ ፍላጎቶቻቸውንም አትከተል አላህም ወደ አንተ ባወረደው ከከፊሉ እንዳያሳስትህ ተጠንቀቃቸው ቢዞሩም አላህ የሚሻው በከፊሉ ኃጢያታቸው ሊቀጣቸው መሆኑን ዕወቅ ከሰዎቹም ብዙዎች አመጠኞች ናቸው:: ሱራ 5፥49 ከዚህ የቁርዓን ጥቅስ የምንረዳው ፍርድ ስናደርግ በአድሎና በሰዎች ፍላጎት ላይ ተመስርተን ሳይሆን በሙሴ ህግ መሠረት መፈፀም እንዳለበት ነው:: በቅርቡ መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ ደጋግሜ እንዳስብና እዳሰላስል የሚያደርግ ቃል አገኘሁ ጌታ ኢየሱስ /ዒሳ/ የፈርሳውያን ሕይወት በሚዘልፍበት ጊዜ የተናገረው ነው:: እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ከአዝሙዝድ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋንኛ የሆኑትን ማለትም ፍትሕን ምህረትንና ታማኝነትን ግን ንቃችኋልና እነዚያን ሳትተው እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር እናንተ የታወራችሁ መሪዎች ትንኝን አጥርታችሁ

ትጥላላችሁ ግመልን ግን ትውጣላችሁ ። እኛ አማኞች እንደ እግዚአብሔር ቃል የመኖር ግዴታ አለብን። ማቴ. 23፥23-24

ወደ አንተ መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አውረድን በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል ከናንተ ለሁሉም ሕግና መንገድ አደረግን አላህ በሻ ኑሮ ሥራዎችንም ለመስራት ተሽቀዳደሙ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው። በርሱም ትለያዩበት የነበራችሁበትን ነገር ይነግራችኋል።ሱራ 5፥48 ቁርዓን ለምን ወረደ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከቁርዓን በፊት የወረዱትን ተውራት ዘቡር ኢንጂል አለመበረዛቸው ትክክል መሆናቸው ለሰው ሁሉ ለማሳወቅ ነው።

እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደወን እስከምታቆሙ /እስከምታሠሩባቸው/ ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው ከጌታህም ወደ አንተ የተወረደው ቁርዓን ከነሱ ብዙዎቹን ትዕቢትንና ክህደትን በእርግጥ ይጨምርባቸዋል በከሐዲያን ሕዝቦችም ላይ አትዘን ። ሱራ 5፡68

በዚህኛው ሱራ እንዳነበብነው ተውራትና ኢንጂል ተበርዘዋል ሳይሆን የሚለው የመጽሐፉ ባለቤቶች መጽሐፉ እንደሚለው መኖር አልቻላችሁም እንደ ቃሉ እስካልኖራችሁ ድረስ አይደላችሁም ወይም አይሳካላችሁም ይለናል። ማሳሰቢያው የሚያተኩረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ኑሩ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም አስቀድሞ ምክሩን ለግሶናል። የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ይህ አትርሱ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን ። ምክንያቱም የሰው ቁጣ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሰው ሕይወት ውስጥ ፍፁም እንዲሆን አያደርግም። ስለዚህ

ርኩሰትንና የክፋትን ብዛት ሁሉ አስወግዳችሁ እግዚአብሔር በልባችሁ የተከለውንና ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለው ቃል በትሕትና ተቀበሉ።

ቃሉን በሥራ ላይ የምታውሉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያታለላችሁ ሰሚዎች ብቻ አትሁኑ። ቃሉን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለው ሰው የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት እንደሚያይ ሰው ነው። ምክንያቱም ይህ ሰው ፊቱን በመስታወት ካየ በኋላ ይሄዳል እንዴት እንደሆነም ወዲያውኑ ይረሳዋል። ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ ተመልክቶ በእርሱ የሚጸና እርሱንም ሰምቶ መርሳት ሳይሆን በሥራ ላይ የሚያውለው ሰው በሥራው የተባረከ ነው። ያቆብ 1፥19-25

እናንተ ያመናችሁ ሆይ በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍዎቹም በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ በአላህና በመላእክቱም በመጽሐፍቹም በመልክተኞቹም በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው ከእውነት የራቀ መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ። እነዚያ በሙሳ ያመኑና ከዚያም ወይፈንን በመስራት የካዱ ከዚያም በርሱ ያመኑ ከዚያም በዒሳ የካዱ ከዚያም በመሐመድ ክሕደትን የጨመሩ አላህ ለእነርሱ የሚምራቸውና ቅኑን መንገድ የሚመራቸው አይደለም። ሱራ 4፥136-137

እነዚህ እነዚያ መጽሐፍትንና ጥበብን ነቢያትንም የሰጠናቸው ናቸው። እነዚህ/የመካ ከሐዲዎች/ በርሷ ቢክዱም በርሷ የማይክዱ ሕዝቦች ለርሷ በእርግጥ አዘጋጅተናል። እነዚህ ነቢያት አላህ የመራቸው ናቸው በመንገዳቸውም ተከተል በእርሱ /በቁርዓን/ ላይ ምንም ዋጋ አልጠየቃችሁም እርሱ ለዓለማት ግሣጼ እንጅ ሌላ አይደለም በላቸው። ሱራ 6፥89-90

እነዚያ መጽሐፍትንና ጥበብን ነቢያትንም ሰጠናቸው የሚለው የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ነቢያትን ማመልከቱ ነው። ነቢዩ

መሐመድ እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ ብሎ በተነሣ ጊዜ አይሁዳውያን አልተቀበሉትም ያልተቀበሉበት ምክንያት እስራኤላውያን ነቢያት ከመነሳታቸው በፊት ከየት እንደሚነሳ ያውቃሉ ነቢያት ከመወለዳቸው በፊት በሌሎች ነቢያት ሥራቸው ሳይቀር በዝርዝር አስቀድሞ ያውቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሁለት ሰው ታሪክ እንመልከት እስራኤላውያን እንደገና በደል ሠሩ ስለዚህም ፍልስጥኤማውያን አርባ አመት ሙሉ እንዲገዙአቸው እግዚአብሔር ፈቀደ።

በዚያን ዘመን ጾርዓ በምትባል የገጠር ከተማ የሚኖር ማኑኤል የሚባል አንድ ሰው ነበር እርሱም ትውልዱ ከዳን ነገድ ወገን ነበር ሚስቱ መኻን ስለነበረች ልጆች አልወለደችም ለእርስዋም የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ እንዲህ አላት እስከ አሁን ልጆች መውለድ አልቻልሽም ነገር ግን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ፀንሰሽ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ የወይን ጠጅም ሆነ ማንኛውም የተከለከለ ምግብ ከመብላት ተጠንቀቂ ልጅሽም ከተወለደ በኋላ ጠጉሩን በፍፁም እንዳትላጪው ምክንየቱም እርሱ ከሚወለድበት ቀን ጀምሮ ናዝራዊ በመሆን ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል እስራኤንም ከፍልስጥኤማውያን እጅ መታደግ ይጀምራል።

ከዚህ በኋላ ሴቲቱ ሄደች ለባልዋ እንዲህ አለችው አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጥቶ ነበር እንደ እግዚአብሔር መልአክ እጅግ የሚያስፈራ ነበር እኔ ከወዴት እንደመጣ አልጠየቅሁትም እርሱም ስሙን አልነገረኝም ነገር ግን ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ብሎ ነገረኝ እንዲሁም የሚወለደው ልጅ በሕይወቱ ሙሉ በናዝራዊነት ለእግዚአብሔር የተለየ ስለሚሆን የወይን ጠጅም ሆነ ማንኛውንም የሚያስክር መጠጥ ከመጠጣትና ማንኛውንም የተከለከለ ምግብ ከመብላት እንድጠነቀቅ ነግሮኛል።

ከዚህ በኋላ ማኑሄ እግዚአብሔር ሆይ ሕፃኑ ሲወለድ ምን ማድረግ እንደ ሚገባን ይነግረን ዘንድ ያ የላከኸውን የእግዚአብሔር

ሰው እንደገና ተመልሶ ወደ እኛ እንዲመጣ አድርግልን ሲል ወደ እግዚአብሔር ፀለየ::

እግዚአብሔርም የማኑሄን ፀሎት ሰማ የእግዚአብሔርም መልአክ እንደገና ወጥቶ ለሴቲቱ በእርሻ ውስጥ እንደተቀመጠች ተገለጠላት ባልዋ ማኑሄ ከእርሷ ጋር አልነበረም ስለዚህ በፍጥነት ወደ እርሱ ሮጣ በመሄድ ተመልከት ያ ከዚህ በፊት ወደ እኔ መጥቶ የነበረው ሰው ዛሬም እንደገና ተገለጠልኝ አለችው::

ማኑሄ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሚስቱን ተከትሎ ሄደ ወደ ሰውየውም ቀርቦ ከሚስቴ ጋር ተነጋግረህ የነበረው አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው :: ሰውየውም አዎን እኔ ነኝ ሲል መለሰ ቀጥሎም ማኑሄ የተናገርከው ቃል ሲፈፀም የሚወለደው ልጅ ምን ማድረግ አለበት? መኖር የሚገባውስ እንዴት ነው ሲል ጠየቀው::

መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ ሚስትህ የነገርኳትን ሁሉ በጥንቃቄ ለመፈፀም እርግጠኛ መሆን አለባት ከወይን ተክል የሚገኝ ምንም ነገር መመገብ አይኖርባትም የወይን ጠጅ ሆነ ማንኛውም የሚያሰክር መጠጥ አትጠጣም ማንኛውንም የተከለከለ ምግብ አተበላም በአጠቃላይ እኔ የነገርኹትን ሁሉ መፈፀም አለባት:: ይህን ሁሉ ሲሆን ማኑሄ ያ ሰው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን አላወቀም ነበር ስለዚህም እባክህን በቶሎ አትሂድብን አንድ የፍየል ጠቦት አርደን እናዘጋጅልህ አለው:: መልአኩም ቢቆይም እንኳ የአንተን ምግብ አልበላም ይሁን እንጂ ልታዘጋጀው ከፈቀድህ የሚቃጠል መስዋዕት አድርገህ ለእግዚአብሔር አቅርበው አለው::

ማኑሄ የተናገርከው ቃል ሲፈጸም ምስጋና እናቀርብልህ ዘንድ ስምህ ማን እንደሆነ ንገረን አለው:: መልአኩም ስሜን ለማወቅ የፈለከው ለምንድን ነው ስሜ ድንቅ የሆነ ምስጢራዊ ነው ሲል መለሰለት:: ከዚህ በኋላ ማኑሄ አንድ የፍየል ጥቦትና የእህል ቁርባን ወስዶ በአለቱ መሰዊያ ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጉ

አቀረበ ማኑሄና ሚስቱም እየተመለከቱ ሳለ እግዚአብሔር አስደናቂ ነገር አደረገ የእሳት ነበልባል ከመሰዊያው ወደ ላይ በሚወጣበት ጊዜ ማኑሄና ሚስቱ የእግዚአብሔር መልአክ በነበልባሉ ውስጥ ወደ ሰማይ ስወጣ አዩ ማኑሄም በዚህ ጊዜ ያ ሰው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ተገነዘበ እርሱና ሚስቱ በግንባራቸው ወደ መሬት ተደፉ ዳግመኛም መልአኩንም አላዩትም።

ማኑሄ ሚስቱን እግዚአብሔርን ስለ አየን በእርግጥ እንሞታለን አላት ሚስቱ ግን እግዚአብሔር ሊገድለን ቢፈልግ ኖሮ መሥዋዕታችንንና ቁርባናችንን ባልተቀበለም ነበር ይህን ሁሉ አሁን ባላሳየንና እንዲህ ያለው ነገር ሁሉ ባልነገረንም ነበር ስትል መለሰችለት።

ሴቲቱም ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሳምሶን ብላ ጠራችው ሕፃኑም አደገ እግዚአብሔርም ባረከው በጸርዓና በኤርሽታኦል መካከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ በነበረበት ጊዜ የእግዜአብሔር ኀይል ያበረታው ጀመር። መሳ. 13፥1-25

የሳምሶን ወላጆች ገበሬዎች ናቸው የሳምሶን የሕይወት ታሪክ የሚጀምረው በዚሁ በእርሻ ነው።በእርሻ ሥራ ላይ ሳለች መልአኩ ተገልጦ እርሷ ምን ማድረግ እንዳለባት የልጁም ማንነት ተነግሮአታል መፈፀም ያለበትና የሌለበት ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሆነ ቤተሰቡ አውቋል።

የሳምሶንን ታሪክ በሰፊው እንድናይ የፈለኩበት ምክንያት እግዚአብሔር አንድን ሰው ለተለየ አላማ ሲመርጠው አስቀድሞ የእግዚአብሔር ህዝብ ሁሉ ያውቃል ነቢይ እግዚአብሔር ሥያስነሳ አይሁዳወያን ሁሉ ያውቃሉ ምክንያቱም አስቀድመው ስለ ሚመጣው ነቢይ ሰምተዋልና ሰውየው እኔ ነብይ ነኝ ብሎ ሰዎችን ለማሳመን ግብግብ አይፈጥርም። አስቀድሞ የተወሰነለትን ሥራ ሰርቶ ይሄዳል።

ሌላው እግዚአብሔር ለተለየ አላማ የፈለገው በነብያት እና በመልአኩ ገብርኤል የተነገረለት ሰው መጥምቁ ዮሐንስ ነው።

ነገር ግን ታላቅና አስፈሪ የሆነው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ነብዩ ኤልያስን ወደ እናንተ እልክላችኋለሁ እርሱም መጥቼ ምድራችሁን እንዳላጠፋ ተለያይተው የነበሩትን አባቶችና ልጆች ልብ ለልብ እንዲቀራረቡ ያደርጋቸዋል ት.ሚል. 4፥5-6 ነብዩ ሚልክያስ በተናገረው መሰረት ሄሮድስ በይሁዳ አገር ንጉስ በሆነበት ዘመን ከአብያ የክህነት ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል ካህን ነበረ እርሱ ከአሮን ዘር የምትወለድ ኤልሳቤጥ የምትባል ሚስት ነበረችው ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ፃድቃን ነበሩ የጌታንም ትእዛዝና ሕግ ያለ ነቀፋ ይጠብቁ ነበር ኤልሳቤጥ መካን ስለሆነች ልጅ አልነበራቸውም ደግሞ ሁለቱም በጣም አርጅተው ነበር።

በዚያን ጊዜ የዘካርያስ የክህነት ሥራ ቡድን ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ተረኛ ነበር ስለዚህ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት የክነቱን አገልግሎት በመፈፀም ላይ ነበር እንደ ክህናት አሰራር ደንብ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገብቶ እጣን ለማጠን ዕጣ ደረሰው በቤተመቅደሱም ዕጣን በሚታጠንበት ጊዜ ህዝቡ ሁሉ በውጪ ቆመው ይፀልዩ ነበር የእግዚአብሔር መልአክ ዕጣን በሚጤስበት መሰዊያ በስተቀኝ በኩል ቆሞ ለዘካርያስ ታየው። ዘካሪያስ መልአኩን ባየው ጊዜ ደንግጦ በፍርሀት ተዋጠ። መልአኩ ግን እንዲህ አለው ዘካርያስ ሆይ አትፍራ ጸሎትህ ተሰምቶልሀል ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሀለች ስሙንም ዩሐንስ ብለህ ትጠራዋለህ የእርሱ መወለድ ለአንተ ተድላና ደስታ ይሆንልሀል ብዙዎች በመወለዱ እንዲሁ ደስ ይላቸዋል። ምክንያቱም እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል የወይን ጠጅና ሌላም የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ገና በእናቱ ማህፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ይሆናል እርሱ ከእስራኤል ህዝብ ብዙዎቹን ወደ እግዚአብሔር ወደ

አምላካቸው ይመልሳቸዋል በመንፈስና በሀይል እንደ ነብዩ ኤልያስ ሆኖ ሕዝቡን ለጌታ ያዘጋጃል እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው የማይታዘዙትንም ሰዎች ልብ ወደ ፃድቃን ጥበብ ይመልሳል ሉቃ. 1፥5-17

ኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰና ወንድ ልጅ ወለደች ጎረቤቶቸዋና ዘመዶችዋ ሁሉ እግዚአብሔር ምህረትን እንዳደረገለት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ተደሰቱ።

ሕፃኑም በተወለደ በስምንተኛው ቀን በግዝረቱ ሥነርዓት ላይ ለመገኘት ጐረቤቶች ዋና ዘመዶችዋ ተሰብስበው መጡ ባባቱም ስም ዘካርያስ ብለው ሊጠሩት ፈልገው ነበር እናቱ ግን እንዲህ አይሆንም ስሙ ዩሐንስ ነው አለች።

እነርሱም ከዘመዶችሽ በዚህ ስም የተጠራ ማንም የለም እኮ? አሉአት ከዚህም በኋላ አባቱን ልጅህ ማን ተብሎ እንዲጠራ ትፈልጋለህ? ብለው በምልክት ጠየቁት።

ዘካርያስም መጻፊያ እንዲሰጡት ጠይቆ ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ ሁሉም በዚህ ነገር ተደነቁ በዚያኑ ጊዜ ዘካርያስ ምላሱ ተፈትቶለት መናገር ቻለ እግዚአብሔርንም ማመስገን ጀመረ። ከዚህ የነሣ በጐረቤቶቻቸው ሁሉ ፍርሀት አደረባቸው ዜናውም በተራራማው በይሁዳ አገር ሁሉ ተሰማ። ይህን ነገር የሰሙ ሁሉ ይህ ህፃን ምን ይሆን እያሉ ይጠይቁ ነበር። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ረድኤት በእርግጥ ከእርሱ ጋር ስለነበር ነው።

እስከ አሁን ባየነው የነቢዩ አነሳስ እና ተግባር በተመለከተ ግንዛቤ እንዳገኛችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ባለፋት ዘመናት ቢሆን በእኛ ዘመን ብዙዎች ነቢይ ነኝ ብለው ተነስተዋል። ነቢይ ነቢይነቱን የሚታወቀው የተናገረው ቃል ሲፈፀም ነው። ከዚህ ወጪ ሌላ የመለኪያ መስፈርት የለውም።

ከዚህ በኋላ ሙሴ እንዲህ አለ ሄዳችሁ በምትወርሱአት ምድር የሚኖሩ አረማውያን ሕዝብ የሟርተኞችንና ሞራ እየገለጡ የዕድልን ምልክትን እንነግራለን የሚሉ አስማተኞችን ምክር ያዳምጣሉ እናንተ ግን ይህን ታደርጉ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር አይፈቅድላችሁም እግዚአብሔር ከወገኖቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነብይ መርጦ ያስነሳላችኋል እርሱ የሚላችሁንም ሁሉ በመስማት ታዛዥ ሁኑ።

በሲና ተራራ ላይ በተሰበሰባችሁበት ቀን እንሞታለን ብላችሁ በመፍራት እግዚአብሔር ዳግመኛ እንዳይናገራችሁና የመገለጡን ሁኔታ የሚያመለክተውን አስፈሪ እሳት እንዳታዩ ጠይቃችሁት ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ጥያቄአቸው ተገቢ ነው።

ስለዚህም እንደ አንተ ያለ ሌላ ነቢይ ከሕዝባቸው መካከል አስነሣላቸዋለሁ እርሱ የሚናገረውን ቃል እሰጠዋለሁ እኔም የማዝዘውን ሁሉ ለሕዝብ ይናገራል እርሱ በእኔ ስም ይናገራል ስለዚህ ለእርሱ የማይታዘዙትን ሁሉ እቀጣለሁ።ነገር ግን ሌላ ነቢይ እኔ ሳላዘው በስሜ ትንቢት ለመናገር ቢደፍር በሞት ይቀጣል እንዲሁም በባእዳን አማልእክት ስም ትንቢት ለመናገር የሚሞክር ለማናቸውም ነቢይ እንዲሁ በሞት ይቀጣል።

አንድ ነቢይ የሚናገረው የትንቢት ቃል ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ መሆኑን በምን ለይተን እናውቃለን? በማለት ትደነቁ ይሆናል። አንድ ነቢይ በእግዚአብሔር ስም ትንቢት ተናግሮ ቃሉ ሳይፈፀም ቢቀር ያትንቢት ከእግዚአብሔር የተሰጠ አይደለም ያ ነቢይ ትንቢቱን የተናገረው በገዛ ሥልጣኑ ስለሆነ ልትፈሩት አይገባም ። ዘዳ. 18፥14-22

እንደ እኔ ያለ ነቢዩ ያስነሳላችኋል የሚለው ብዙዎች በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል ሙሴ ለሕዝብ ያስተላለፈው መልእክት እኔ ከሞትሁ በኋላ በእኔ የሚተካ ሰው እግዚአብሔር ያስነሳላችኋል ማለቱ

ነው:: አንዳንድ ሰዎች ይህ ትንቢታዊ መልእክት ለነቢዩ ለመሐመድ የተባለ ነው ይላሉ::

ሙሴ በእድሜው አርጅቶ ስለ ነበር በእርሱ እግር ገብቶ እስራኤልን የሚመራው ግለሰብ አስመልክቶ የተነገረ ነው እንጂ ሌላ ሰውን አያመለክትም::

ሙሴ ንግግሩን በመቀጠል ለእስራኤል ሕዝብ እንዲህ አለ እነሆ የእኔ ዕድሜ መቶ ሃያ ዓመት ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ እናንተን መምራት አይቻለኝም ከዚህም በላይ እኔ ዮርዳኖስን እንደማልሻገር እግዚአብሔር ነግሮኛል አምላካችሁ እግዚአብሔር ራሱ በፊታችሁ እየሄደ ይመራችኋል :: በዚያን የሚኖሩትን አሕዛብ ስለሚደመስሳችሁ ምድራቸውን ትወርሳለችሁ እግዚአብሔር በተናገረው መሰረት ኢያሱ መሪያችሁ ይሆናል:: እግዚአብሔር አሞራውያንን እንዳጠፋ የእናንተ ጠላቶች የሆኑትን ሕዝብ ይደመስሳችኋል:: እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ድልን ያጐናጽፋችኋል ስለዚህ ልክ እኔ የነገርኋችሁን ሁሉ በእነርሱ ላይ ታደርጉባቸዋላችሁ:: ቆራጥነትና ድፍረት ይኑራችሁ ከእነርሱም የተነሣ ክቶ አትፍሩ አትደንግጡም ምክንያቱም ራሱ አምለካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል አይጥላችሁም አይለያችሁም::

ከዚህ በኋላ ሙሴ ኢያሱን ጠርቶ በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፊት እንዲህ አለው ቆራጥነትና ድፍረት ይኑርህ እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶቻቸው በሰጣቸው ተስፋ መሰረት ምድሪቱን ይወርሱ ዘንድ እነዚህን ሕዝብ መርተህ የሚታስገባ አንተ ነህ ራሱ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በመሆን ይመራሀል አይጥልህም ከቶም አይተውህም ስለዚህ ወኔህ አይቀዝቅዝ ልብህም አይፍራ:: ዘዳግም 31፥1-8

የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ወጥቶ በምድረ በዳ ለአርባ አመታት ተንከራትተዋል እግዚአብሔርን ባለ መታዘዛቸው ምክንያት

ከግብፅ የወጣው ሕዝብ ሁሉ አልቆአል። በምድረ በዳ የተወለደው አዲሱ ትውልድ በኢያሱ መሪነት ለአባቶቻቸው ወደ ተሰጠው ተስፋ ምድር እንድገቡ የተሰጠውን ትዕዛዝ ነው የተመለከትነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልተበረዘ ትክክል እንደ ሆነ የሚናገሩትን የቁርዓን ጥቅሶችን እንመልከት ከአንተ በፊት ወደነሱ ወሕይን /ራእይን /የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም የማታውቀም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ ሱራ 16፥43

ቁርዓን ለሙስሊም ወገኖቻችን የሰጠው ትዕዛዝ ራዕይ ያወረድንላቸው ክርስቲያንኖችን የማታውቀውን ጠይቀህ ከእነርሱ ተረዳ ብሎአል እስከ አሁን ድረስ ሙስሊም ወንድሞቻችን የቅዱስ ቁርዓን ትዕዛዝ አልተገበሩትም ወደ ፊት አላህ ይህን ትዕዛዝ የሚፈፅሙ አዲስ ትውልድ ያስነሳል ብዬ አስባለሁ።

ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡት ጠይቅ እውነቱን ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሀል ከተጠራጣሪዎችም አትኹን ሱራ 10፥49

በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ መጽሐፍትን ትመረምራላችሁ እነዚህ መጽሐፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው። እናንተ ግን ሕይወት እንድኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም።

ዮሐ.5፥39-40

በአንተ በፊት በነበሩበት በመጀሪያዎቹ ሕዝቦች ውስጥ መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል ሱራ 15፥10

ከበፊትም መልክትኛ በእርግጥ ተስተባበሉትም ነገርና በተሰቃዩት ላይ እርዳታችን እስኪመጣላቸው ድረስ ታገሱ የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ ከመልእክተኞቹም ወሬ የምትረጋጋበት በእርግጥ

መጣልህ ሱራ 6፥34 የአዲስ ኪዳን ነቢያቶች እና መልእክተኞች እኛ እስክንመጣላቸው ድረስ በመከራ ውስጥ አልፈው መከራን ታግሰዋል የእግዚአብሔር ቃል እነርሱም አልበረዙትም ሌላውም እንዳይበርዝ ጠብቀውታል ነው የሚለው ቁርዓን፡፡

ለነርሱ በቅርበቱ ሕይወትም በመጨረሻይቱም ብስራት አላቸው የአላህ ቃላት መለዋወጥ የላትም ይህ እርሱ በታላቅ እድል ነው፡፡ ሱራ 10፥64 በእርግጥ ነው የእግዚአብሔር ቃል አያልፍም፡፡

የጌታህም ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትኾን ተፈጸመች ለቃላቱ ለዋጭ የለም እርሱም ሰሚው ዐዋቂ ነው፡፡ ሱራ 6፥115 ተውራትና እንጂል የአላህ ቃል በመሆናቸው አይለወጡም ማለት ነው ፡፡

ከጌታህም መጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ ለቃላቶቹ ለዋጭ የላቸውም ከርሱ በቀር መጠጊያ በፍጹም አታገኝም፡፡ ሱራ 18፥27

ሙስልም ወንድሞቻችን መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል አይደለም ተበርዟል የሚሉት ከየት አምጥተው ነው እስከ አሁን በተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ እና ያልተበረዘ መሆኑ ከነማስረጃ በሰፊው ተመልክተናል እንዲያውም የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም ከእርሱ በቀር መጠጊያ የለም በሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማስማማት የርዕርሱ መቋጫ ይሆነናል፡፡

በአንተ በመታመናቸው በዓለማቸው ለጸኑ ሁሉ ፍጹም የሆነውን ሰላምህን ትሰጣቸዋለህ፡፡ ለዘላለሙ በእግዚአብሔር ታምናችሁ ኑሩ ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም መጠጊያ አንባችን ነው፡፡ ኢሳ. 26፥3-4

## 1. ይቅርታ

የኃጢአት ሥርየት በተመከተ ያላቸው መረዳት የዕዳ ጫና መሠረዝ ከከባድ ሸክም መላቀቅ:: ከጭንቀትና ከመሳቀቅ ነፃ መሆን:: ከአላህ ዘንድ ይቅርታ ወይም የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት ግለሰቡ ብርቱ ጥረት ማድረግ አለበት::

ከእግዚአብሔር ቃል ዳዊት የፀለየው ፀሎት አምላክ ሆይ ስለ ዘላለማዊ ፍቅርህ ይቅር በለኝ ስለ ታላቁ ምህረትህም ኃጢያአቴን ደምስስልኝ:: በደሌን ሁሉ አጥበህ አስወግድልኝ ከኃጢያአቴም አንጻኝ:: እኔ ስህተቴን አውቃለሁ የኃጢያአቴንም ብዛት ዘወትር እገነዘባለሁ:: መዝ. 51፥1-3

በእናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበርን ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ አላህ ኃጢያቶችን በመላ ይምራልና እነሆ እርሱ መሐሪ አዛኝም ነውና ::

ሱራ 39፥53

አላህ በርሱ ማጋራትን በፍፁም አይምርም ከዚህ ሌላ ያለውንም /ኃጢአት/ለሚሻው ሰው ይምራል:: በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅ ኃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ::

አዳኝ ኃጢያአትን ማስተሰረይ የሚችል በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ገብቶ የሚያስታርቅ አስፈላጊ አይደለም::

ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ ኾናችሁ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ ኾናችሁ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ ለየብቻችሁ ኾናችሁ በእርግጥ መጣችሁን እነዚያንም እነሱ በናንተ ውስጥ /ለአላህ/ ተጋሪዎቹ ናቸው የምትሉአቸውን አማላጆቻችሁን ከናንተ ጋር

አናይም ግንኙነታችሁ በእርግጥ ተቋረጠ ከናንተም ያ/ያማልደናል/ የምትሉት ጠፋ /ይባላል/ ሱራ 6፥104

ልጆቼ ሆይ ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሰሩ ብዬ ነው፡፡ ነገር ግን ማንም ሰው ኃጢአት ቢሰራ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኃጢያአታችንም የሚደመሰሰው በእርሱ ነው የእኛ ኃጢያአት ብቻ ሳይሆን የዓለሙም ሁሉ ኃጢያአት የሚደመሰሰው በእርሱ ነው፡፡ 1ዮሐንስ 2፥1-2 ዒሳን የተመለከቱ ሰዎች ሁሉ ሩህሩህ ይቅር የሚል መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ በማግስቱም ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው፡፡ዮሐ. 1፥29

## *<u>በሙስሊሞች ዘንድ ይቅርታ የሌለው ኃጢአት</u>*

- የፈጣሪ ስልጣንና ሀይል የሚጋራ፣ አምላክ ራሱን በተለያዩ አካላት ገልጧል ብሎ ያመነ እና የተናገረ፡፡ ሱራ 4፥116፣5፥72-73
- ልቡ እያወቀ ከእምነት ወደ ኋላ ማለትና በነቢዩ ከተገለጠው እምነት ሌላ ጨምሮ መቀበል ሱራ 3፥86-87፣3፥90
- አማኝን ያለ አግባቢ መግደል ሱራ 4፥193

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች እስላሞች በፅኑ የብረት አጥር ውስጥ ከበው ስለ አስቀመጡት ሙስሊሞችን ወደ ጌታ መምጣት ከባድና ውስብስብ ሆኖ ይታያል፡፡

## VIII. *ምስክርነትህን በጥያቄ ጀምር*

በዚህ ርዕስ መግቢያ አንተን በመጠየቅ ልጀምር ጥያቄ ምልክት የሌለባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው? ለመጀመሪያ ጊዜ ጥያቄ የጠየቀው ማነው፡፡ ሁለተኛውስ ጠያቂ ማነው፡፡

ይህ ጥያቄ በውስጤ ሲፈጠር መልሱን ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱሴን ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ጀምሮ ማንበብ ጀመርኩኝ:: በምዕራፍ አንድ ሁለት ቃሎችን አግኝቼ አለሁኝ::

አንደኛው ትዕዛዛዊ ቃል ይሁን የሚል ነው እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ ሆኖም ሌላው ትዕዛዛዊ ቃል ይግዙ የሚለው ለአዳምና ለሔዋን የተሰጣቸው ስልጣን ነው:: በተመሳሳይ በምዕራፍ ሁለት የተሰጠ ትዕዛዛዊ ቃል

ደጉንና ክፉውን ለመለየት የሚያስችል እውቀት ከሚሰጠው የዛፍ ፍሬ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ::

በሁለቱም ምዕራፎች ለጥያቄ መልስ ስላላገኘሁ ወደ ሦስተኛው ምዕራፍ መሻገር ነበረብኝ::

ዘፍ. 3፥1 እግዚአብሔር ከፈጠራቸው አራዊት ሁሉ እባብ እጅግ ተንኮለኛ ነበረ:: ስለዚህ እባብ በአትክልቱ ቦታ ካሉት ዛፎች ሁሉ ፍሬ እንዳትበሉ በእርግጥ አዝዞአችኋልን ሲል ሴቲቱን ጠየቃት::

ጥያቄ መጠየቅ መቼ ተጀመረ ለሚለው መልሱ በፍጥረት መጀመሪያ በኤደን ገነት የመጀመሪያው ጥያቄ ጠያቅ ሰይጣን ነው:: የጥያቄ ምልክት የሌለባቸው ምዕራፎች ዘፍ. 1 እና 2 ናቸው::

ሰይጣን ከሄዋን ጋር በኤደን ገነት ሲወያይ አንድም ቃል መልካም ነገር አልወጣውም ምክንያቱ ግልፅ ነው:: በሰይጣን ማንነት መልካም ነገር ተፈልጎ ስለማይገኝበት ነው::

እንዲያውም ማንነቱን ስገልፅ ተንኮለኛ ነበር በማለት ይጀምራል ሰይጣን ከሰዎች ጋር ከተወዳጀ ሰዎቹ ሁሉም ተንኮለኞች ነው የሚሆኑት:: ተንኮለኞች ባሉበት ሰላም ፍቅር አንድነት አይኖርም:: ሁለተኛው ጠያቅ እግዚአብሔር ነው::

በዚያን ቀን ምሽት እግዚአብሔር አምላክ በአትክልቱ ቦታ ውስጥ ሲመላለስ ድምፁን ሰሙ ስለዚህም አዳምና ሚስቱ

እግዚአብሔር አምላክ እንዳያያቸው በዛፎች መካከል ተደበቁ የት ነው ያለኸው? ሲል ጠይቀው::

ከዚህ በኋላ የሰው በምክንያት የታጨቀ ሀሳቡን መግለፅ የጀመረበት ክስተቱ ተፈጠረ እርሷ ነች እርሱ ነው የሚባሉት ቃላቶችን መጠቀም ጀመሩ::

የአዳም ልጆች አንዱ በሌለው ላይ ተነስቶ ገደለው እግዚአብሔር ለአባቱ ለአዳም የጠየቀው ጥያቄ መልሶ ለልጁ ቃየል ጠይቆታል:: ከዚህ በኋላ ቃየልና ወንድሙ አቤል ወደ ሜዳ በሄዱ ጊዜ ቃየል በጠላትነት ተነሥቶ ወንድሙ አቤልን ገደለው:: እግዚአብሔርም ቃየልን ወንድም ወዴት ነው? ሲል ጠየቀው ቃየልም የት እንዳለ አላወቅም እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን? ብሎ መለሰ:: ዘፍ. 4፡8-9

ከእነዚህ ክስተቶች በኋላ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ በጥያቄ የተሞላ ሆነ በዳዊት ሕይወት የነበሩት ጥያቄዎች ጥቂቶችን እንመልከት :: ሰዎች ለብዙ ጊዜ የቆየ ጥያቄ በውስጣቸው ስኖር ከውስጣቸው ሁለት ቃላቶች ይወጣሉ እስከ መቼ

ዳዊትም የውስጡን ችግር እንዲህ ገልጦታል ::

እስከ መቼ ክብሬን ታዋርዳላችሁ?

እስከ መቼ ከንቱ ነገርን ትወዳላችሁ?

እስከ መቼ ሐሰትን ትፈልጋላችሁ?

በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ የዳዊት ጥያቄ

አንድ ነገር ብቻ እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን ለመንሁት የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም በህይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እንድኖር በዚያም ሆኜ የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳደንቅ አመፉሩንም እንድጠይቅ ነው:: መዝ. 27፡4

አንድ ሀብታም ሰው ለጌታ ለኢየሱስ የጠየቀው ጥያቄ የሰው ሁሉ ጥያቄ መሆን አለበት::

ከአይሁድ አለቆች አንዱ ኢየሱስን ደግ መምህር ሆይ ! የዘላለም ህይወትን ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባኛል ብሎ ጠየቀው ፡፡ ሉቃ. 18፥18

ፊልጶስ ከኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ጋር ተገናኝቶ ወንጌልን ለመስበክ ለመግቢያ የተጠቀመበት መንገድ ጥያቄ በማንሳት ነው የጀመረው፡፡

የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን ተነሥና ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚወስደው መንገድ ወደ ደቡብ ሂድ አለው ፡፡ ያ መንገድ የበረሀ መንገድ ነበረ፡፡ እርሱም ተነስቶ ሄደ፡፡ እነሆ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር ይህ ሰው ህንደኬ ለተባለች ለኢትዮጵያ ንግሥት ባል ሟልና የገንዘቧ አዛዥ ነበረ፡፡

እርሱ ወደ አገሩ ሲመለስ በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩ የኢሳያስ መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሂድ ወደ ሰረገላው ቅረብ አለው፡፡ ስለዚህ ፊልጶስ ወደዚያ ሮጦ ሄደና ኢትዮጵያዊ የነብዩ መጽሐፍ ሲያነብ ሰምቶ የምታነበው ትርጉም ይገባሀልን? አለው የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት ሊገባኝ ይችላል?አለና ፊልጶስን ወደ ሰረገላ ውጣና ከእኔ ጋር ተቀመጥ አለው ፡፡ ጃንደረባውም ያነበው የነበረው የመጽሐፍ ክፍል ይህ ነበረ፡፡

ለመታረድ እንደሚነዳ በግ ነበረ ሲሸልቱት ዝም እንደሚልጥቦት እርሱም ለመናገር አፉን አልከፈተም፡፡ እርሱ ተዋረደ ቅን ፍርድም አልተሰጠውም ጀንደረባውም ፊልጶስም ከዚህ ምጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ መልካሙን ዜና አበሰረው ፡፡ሐዋ. 8፥26-35

የምታነበውን ታስተውለዋለህ ?

እኛም ለራሳችን ለምስክርነት የሚረዱን መንገዶችን ፈጥረን መጠየቅ አለብን፡፡

- የአማኞች /የጴንጤዎች/ መንፈሳዊ መዝሙር ሰምተህ ታውቃለህ?
- መዝሙሩን ሥትሰማ ምን ተሰማህ?
- አሁን መዝሙር መስማት ትፈልጋለህ? ልስጥህ /ላውስህ/
- የመዝሙር ካሴቱን ሰምተህ እንደወደድኸው ነግረኸኛል ለምን ዘማሪዎች ሲዘምሩ በአካል ተገኝተህ አታያቸውም።
- ስለ አላህ አስበህ ታውቃለህ?
- በግልህ ታውቀዋለህ ?
- እግዚአብሔርን ማወቅ ይቻላል ብለህ ታስባለህ?
- በሃይማኖትህ የተሰጠህን ትዕዛዝ ትፈፅማለህ?
- እግዚአብሔርን/አላህን/ በዚህ ዘመን ማነጋገር ይቻላል?ወይስ?
- ፀሎትህን እንደ ሚሰማህ ታምናለህ?
- ለአንተ በግልህ ይጠነቀቅልሀል?
- ችግር ሲገጥምህ ግድ ይለዋል?
- ለፀሎትህ መልስ ሰጥቶህ ያውቃል?
- እግዚአብሄር ይናገራል የሚል ከሆነ በህልም ተናግሮህ ያውቃል?
- ጂኒን ትፈራለህ?
- ጂኒ ቢመታህ ምን ታደርጋለህ?
- በጂኒ ስልጣን ያለው ማን ነው?
- ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር አለህ?
- የወደፊት ተስፋህ ምንድን ነው?
- በኢንጅል ታምናለህ ካመንህ በቤትህ ኢንጂል አለህ?
- ከሌለህ ልሥጥህ?
- ኢንጂልን አንብበህ ታውቃለህ?

- እግዚአብሔር እንዲያደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለህ ? ፈቃደኛ ከሆንህ ልፀልይልህ?
- ሌላ ልትነግረኝ የሚትፈልገው ካለህ ንገረኝ እና አብረን በጉዳዩ ላይ እንፀልያለን::

ውድ ወገኞች ሆይ ! መቼም ምስክርነት በእግዚአብሔር አሰራር ሆኖ በሰው አንደበት የሚነገር ቢሆንም ቅሉ ለሰው ሁሉ አእምሮ የሚመቸውን ከማድረግ የሚከለክል መንፈስ ያለ አይመስለኝም:: ስለዚህ ግን እኔ ከታየኝ አንፃር ይህንን ብዬአለሁኝ:: ቢሆንም በጎነትን ባሳያችሁ በእግዚአብሔር ፀጋ ተሞልታችሁ ለወንድሞቻችሁ ወንጌል ለማድረስ ባበረከትኩላችሁ ጽሑፍና በእግዚአብሔር መንፈስ አጋዥነት እንድታገለግሉ ይሁን ስል ወንድማዊ ምክሬን እሰጣለሁ ::

*«በዚህ መንጋ ውስጥ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱንም ማምጣት ይገባኛል እነርሱም ድምጼን ይሰማሉ አንድ መንጋም ይሆናሉ ዩሐ 10:16 »*

ዋቢ መጽሐፍት

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ቅዱስ ቁርዓን
- ሐጂ መሐመድ ሣኒ ሐቢብ የጻፉት እስልምና እና የታላቁ ነብይ የሙሐመድ ታሪክ ::
- ሌሎችም በእጄ ያሉ ጽሑፎችን ተጠቅሜአለሁ::